**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

5ki Diro Kiiro …

Hawaasa, Maaja…, 2017 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mininnii Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት የወጣ

፭ኛ ዓመት ቁጥር …

ሀዋሳ ሀምሌ … ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም

**Amado**

**Lallawu Kiiro……./2017**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Jeefisiisaanote Bissa Uurrisatenna Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa …… Qoola …**

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር……./፳፻፲፯**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ …ገጽ ….**

**Lallawu Kiiro……_2017**

**Woyyaawino Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Jeefisiisaanote Bissa Uurrisatenna Biilloonyenna Qeecha Murate Fulino Lallawa**

Qoqqowu mootimmata keeru, latishshu, farcotenna danchu gashshooti mixo jeefisiissanno jeefisaano uurrinshuwa konni albanni fultino lallawubba garinni uurrite loosanni nooti anfoonnita ikkitanna sa'u yanna giddo noo xaphooma ha'rinshonni borreessantinoti kaajja loossa jawaatte suffanno gedenna laanfetenni leeltino

**አዋጅ ቁጥር………./፳፻፲፯**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ**

የክልሉን መንግሥት የሠላም፣ የልማት፣ የፍትህና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶችን የሚያስፈጽሙ አስፈጻሚ አካላት ከዚህ ቀደም በነበሩ አዋጆች ተቋቁመው እየሰሩ እንደሚገኙ የሚታወቅ ሲሆን ባለፉት ጊዜያት ውስጥ በነበረው አጠቃላይ ሂደት የተመዘገቡ ጠንካራ ውጤቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉና በድክመት የተስተዋሉ ጉዳዮች በየወቅቱ

hajubba yanna yannatenni woyyaabbanni hadhanno xaphooma amuraate haruunsa hasiissannota ikkitinohura; Daga mootimmate uytinota xaphooma sokko woyyawino garinni jeefisate dandiisiisanno garinni mootimmate uurrinshubba tantano gobboomunna qoqqowu deerrinni heedhanno soorro kaima assatenni hasishshu garinni yanna yannatenni woyyeessanna uurrinshubba dagoomaho uytanno owaantubba dhuku fajji bikkinni tuqqinnota, hanqaffannota, waaxotenni loosantannotanna jiro garunni horonsi'ra hedote worino garinni ikkansa buuxisa hasiissannohura;

Konni kaiminni qoqqowunnita jeefisiisanno bissa tantano, biilloonyenna loosu qeecha woyyeessanno seera fushsha hasiisinohura Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Amaale mini qoqqowu Bayriidi Seeri quwa 48 cinaancho quwa 3 fidale (a) iima uynoonnisi biilloonyi garinni aaninoha lallawino.

**<u>GAFA MITE</u>**

**<u>Xaphooma Woro</u>**

1. **<u>Harancho Umo</u>**

   Kuni lallawi **"Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Jeefisiisaanote Bissa Uurrisatenna Biilloonyenna Qeecha Murate fulino Lallawi Kiiro …/2017 M.D"** yaamame woshshamara dandaanno.

2. **<u>Tiro</u>**

   Qaalu horo wole tiro uysiissannota ikka hoogguro konni lallawi giddo:

እየተስተካከሉ የሚሄዱበትን አጠቃላይ ሥርዓት መከተል አስፈላጊ በመሆኑ፣

ሕዝቡ ለመንግሥት የሰጠውን አጠቃላይ ተልዕኮ በተሻለ ሁኔታ ለመፈጸም እንዲቻል የመንግሥት ተቋማት አደረጃጀትን በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ የሚኖሩ ለውጦችን መነሻ በማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው መከለስ እና ተቋማቱ ለሕብረተሰቡ የሚሰጧቸው አገልግሎቶች አቅም በፈቀደ መጠን ተደራሽ፣ አካታች፣ በቅንጅት የሚፈጸሙ እና ሀብትን በአግባቡ መጠቀምን ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ስለሚገባ፤

ከዚህም አንጻር የክልሉን አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን የሚያሻሽል የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት በማስፈለጉ, የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ ፫ ፊደል ተራ (ሀ) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሚከተለውን አውጇል፡፡

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   **ይህ አዋጅ "የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር …../፳፻፲፯ ዓ.ም"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

1) **“Qoqqowo”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowoti;
2) **“Qoqqowu amaale mine”** yaa Sidaamu dagoomu qoqqowi mootimma amaale mineeti;
3) **“Jeefisiisaanote Amaale Mine”** yaa konni Lallawira quwa 5 hunda xawinsoonni jeefisiisaanote bissa miiloomimmatenni hanqafino amaalete mineeti;
4) **“Gashshootu Amaale Mine”** yaa Qoqqowu giddo tantanantino zoone, woradu, quchumu gashshootinna olluu deerrinni garisenni tantanantino jeefisiisaanote bissa tantano miila asse hanqafino amaalete mineeti;
5) **“Gashshootu Taqqa”** yaa hasiishshisi garinni qoqqowoho afantanno zoonete, woradu, quchumu, sinu quchuminna baadiyyetenna quchumu olluubba gashshoote amadannoho;
6) **“Biiro”** yaa hasiishshisi garinni lamenna hakkiinni roortinota loosu xintamooshshi handaarra noosetenna qoqqowu jeefisiisaanote amaale minira miila ikkitino jeefisiisaancho uurrinshaati;
7) “**Biilloonye”** yaa mitte mootimmate sokkara addi loosu xintamooshshinni mannu wolqa gashshootinna boobbahishshinni tantanantanno hasiisi garinni qoqqowujeefisiisaanote amaale mini miila assinanni jeefisiisaancho uurrinshaati;
8) “**Komishiine woy Ejense”** yaa mitte mootimmate sokkara xintantannotenna hundaanchimmansa hasiisi garinni soorrantara dandiitanno jeefisiisaancho uurrinshaati;

1) **“ክልል”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፤
2) **“የክልል ምክር ቤት”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ነው፤
3) **“የመስተዳድር ምክር ቤት”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተጠቀሱ አስፈጻሚ አካላትን በአባልነት የያዘ ምክር ቤት ነው፤
4) **“አስተዳደር ምክር ቤት”** ማለት በክልሉ ውስጥ በተደራጀ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር እና በቀበሌ ደረጃ እንደ አግባብነቱ የተደራጁ የአስፈጻሚ ተቋማት አደረጃጀትን በአባልነት የያዘ ምክር ቤት ነው፤
5) **“የአስተዳደር እርከን”** ማለት እንደ አግባብነቱ በክልሉ የሚገኝ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የክፍለ ከተማ እና የገጠርና የከተማ ቀበሌ አስተዳደርን ያጠቃልላል፤
6) **“ቢሮ”** ማለት እንደ አስፈላጊነቱ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የሥራ አደረጃጀት ዘርፎች ያሉትና የመስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆነ አስፈጻሚ ተቋም ነው፤
7) **“ባለሥልጣን”** ማለት ለተወሰነ መንግስታዊ ተልዕኮ በተለየ የሥራ አደረጃጀት፣ የሰው ኃይል አስተዳደርና ስምሪት የሚዋቀር እንደ አስፈላጊነቱ የመስተዳድር ምክር ቤት አባል የሚደረግ አስፈጻሚ ተቋም ነው፤
8) **“ኮሚሽን ወይም ኤጀንሲ“** ማለት ለተወሰነ መንግስታዊ ተልዕኮ የሚደራጅ እና እንደ አስፈላጊነቱ ተጠሪነቱ ሊለወጥ የሚችል አስፈጻሚ ተቋም ነው፤

9) "**Institiyute**" yaa mitte mootimmate sokkara dagoomu qarra tirate xiinxallo assatenni mootimmate muro shiqishshanno mootimmate uurrinshaati;

10) **"Handaara"** yaa mitte jeefisiisaancho uurrinsha giddo mimmito labbanno woy irkisantanno garinni lamenna hakkiinni roortino dayrekterootetenni xintamino qara uurrinshate looso waaxe amadanno uurrinshate loosu tantanoti;

11) **"Dayrektoreete"** yaa mittu dani timo noonsarenna amadantino loossa hasiisi garinni hanafotenni gumu geeshsha jeefisate uurrinshuwate akatta garinni xiinxallatenni kalaqantanno loosu tantanooti;

12) **"Biirote sooreessa"** yaa konni lallawi garinni uurrinsoonni biiro massagate pirezidaantichu shiqishonni sommesi Qoqqowu Amaale Mininni kaajjitanno kalaqamu manchooti;

13) **"Qara dayrektere"** yaa konni lallawi garinni uurrinsoonni biilloonye massagate pirezidaantichunni somamannoha ikke biilloonyu goli qoqqowu jeefisiisaanote mootimma amaale minira miila ikke uurrannoha ikkiro sommesi Qoqqoqu Amaale Mininni kaajjitanno kalaqamu manchooti;

14) **"Komishiinere"** yaa konni lallawi garinni uurrinsoonni komishiine massagate pirezidaantichunni somamannoha ikke komishiine galtannohu Qoqqowu Amaale Mini hunda ikkiro sommesi Qoqqowu Amaale Mininni kaajjitanno kalaqamu manchooti;

9) **"ኢንስቲትዩት"** ማለት በተወሰነ መንግስታዊ ተልዕኮ የህብረተሰብን ችግር ለመፍታት ጥናትና ምርምር በማካሄድ ለመንግስት ውሳኔ የሚያቀርብ መንግስታዊ ተቋም ነው፤

10) **"ዘርፍ"** ማለት በአንድ አስፈጻሚ ተቋም ውስጥ ተቀራራቢ ወይም ተመጋጋቢ በሆነ ሁለትና ከዚያ በላይ ዳይሬክቶሬት የተደራጁ አንኳር ተቋማዊ ተግባራትን አጣምሮ የሚይዝ ተቋማዊ የሥራ አደረጃጀት ነው፤

11) **"ዳይሬክቶሬት"** ማለት አንድ ዓይነት ግብ ያላቸውና የተያያዙ ሥራዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ከጅማሬ እስከ ውጤት ለመፈጸም እንደየተቋም ባህሪ በማጥናት የሚፈጠር የሥራ አደረጃጀት ነው፤

12) **"የቢሮ ኃላፊ"** ማለት በዚህአዋጅ መሠረት የተቋቋመውን ቢሮ ለመምራት በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት ሹመቱ በክልሉ ምክር ቤት የሚጸድቅ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

13) **"ዋና ዳይሬክተር"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመውን ባለሥልጣን ለመምራት በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾም ሆኖ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የመስተዳድር ምክር ቤት አባል ሆኖ የተቋቋመ ሲሆን ሹመቱ በክልሉ ምክር ቤት የሚጸድቅ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

14) **"ኮሚሽነር"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመውን ኮሚሽን ለመምራት በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾም ሆኖ የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለክልል ምክር ቤት ሲሆን ሹመቱ በክልሉ ምክር ቤት የሚጸድቅ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

15) **“Qara loosu ha’risancho”** yaa konni lallawi garinni uurrinsoonni ejense woy inistitiyute massagate pirezidaantichunni somameenna sommesino kaajjitanno kalaqamu manchooti;

16) **“Layinki biirote sooreessi, woy layinki qara dayrektere, woy layinki komishineere, woy layinki loosu ha’risaancho woy handaaru sooreessa”** yaa konni lallawi garinni uurrinsoonni jeefisiisaancho uurrinsha giddo layinki uurrinshate massagaanchimmanni loosara qaru uurrinshate sooreessi shiqisheenna pirezidaantichunni somamanno kalaqamu manchooti;

17) **“Dayrektoreetete dayrektere”** yaa konni lallawi garinni mitte jeefisiisaancho uurrisha giddo dayrektoreete massagate loosu ikkadimma heewonni gaamamannoha woy hasiishu gariinni mootonsineenna (soommeenna) gaamamooshshuno uurrinshate sooreessinni kaajjanno kalaqamu manchooti;

18) ‘’**Baattote gashshoote**’’ yaa baattote amado aana woowe uyinanniha, baattote horonshi mixo loosu aana hossa, baattote horaameyye mereero kalaqantanno kipho tiranni, horaamessu qoossonna gadacho loosu aana hosa, baattote amado animate taje gamba assanna keenne horaameeyyete sayisate amurateti;

19) **“Mancho”** yaa kalaqamu mancho woy seerunni mannimmate qoosso uynoonnisi bisooti;

20) Konni lallawi giddo mitte koo-teemmanni worronnihu wole koo-teemmano amadannoho.

15) **“ዋና ሥራ አስኪያጅ”** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመውን ኤጀንሲ ወይም ኢንስቲትዩት ለመምራት በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾምና ሹመቱም የሚጸድቅ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

16) **“ምክትል የቢሮ ኃላፊ ወይም ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይም ምክትል ኮሚሽነር ወይም ምክትል ሥራ አስኪያጅ ወይም የዘርፍ ኃላፊ”** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በተቋቋመው አስፈጻሚ ተቋም ውስጥ በምክትል የተቋም መሪነት እንዲሰራ በዋና የተቋም ኃላፊ አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾም የተፈጥሮ ሰው ነው፤

17) **“ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር”** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በአንድ አስፈጻሚ ተቋም ውስጥ ያለውን ዳይሬክቶሬት ለመምራት በሜሪት ውድድር የሚመደብ፡ ወይንም እንደ አስፈላጊነቱ በሹመት ሊመደብ የሚችልና ምደባውም በተቋሙ ኃላፊ የሚጸድቅ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

18) **የመሬት አስተዳደር** ማለት በመሬት ይዞታ ላይ ዋስትና የሚሰጥበት፣ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሚፈፀምበት፣ በመሬት ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሳ ግጭት የሚፈታበት፣ የተጠቃሚ መብትና ግዴታ የሚፈፀምበት፣ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት መረጃ የሚሰበሰብበትና ተገምግሞ ለተጠቃሚዎች የሚተላለፍበት ሥርዓት ነው፤

19) **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

20) በዚህ አዋጅ ውስጥ በአንድ ጾታ የተደነገገው ሌላኛውንም ጾታ ያጠቃልላል፡፡

## GAFA LAME

## Pirezidantichu, Layinki Pirezidantichinna Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Mini Biilloonyenna Loosu Qeecha

**3. Pirezidaantichu Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Pirezidaantichu biilloonyinna loosu qeechi Qoqqowu Bayriidi Seeri Quwa 59 aana worroonni garinni ikkanno.

**4. Layinki Pirezidantichi Biillooyenna Loosu Qeecha**

Layinki pirezidantichi biillooyinna loosu qeechisi qoqqowu Bayriidi Seeri Quwa 60 aana worroonni garinni ikkanno.

**5. Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Mini Miilla**

1) Pirezidaanticha;
2) Layiinki prezidaanticha;
3) Konni lallawi quwa 9 garinni uurrinsoonni jeefisiisaano uurrinshuwa sooreeyye;
4) Pirezidaantichu miiloomimmatenni beeqqitara doodhanno wolootu loosu sooreeyye;
5) Konni quwira cinaancho quwa (4) garinni lendanni miilla konni lallawira xintinoonni xaphoomu Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Mini batinyinni sasunni mitte anga aleenni ikka dinonsa;
6) Konni quwi cinaancho quwa (4) aana kulantino jeefisiisaanote uurrinshuwa sooreeyye Jeefisiisaanote Amaale Mini gambooshshira leellate dandiitannokki yannara xawoho uynanni riqiwooshshinni layinki sooreeyye beeqqa dandiitanno.

## ክፍል ሁለት

## ስለ ርዕሰ መስተዳድር፣ ምክትል ርዕስ መስተዳድር እና የመስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

**3. የርዕሰ መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር**

የርዕሰ መስተዳደሩ ሥልጣንና ተግባር በክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፱ ላይ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

**4. የምክትል ርዕስ መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር**

የምክትል ርዕስ መስተዳደሩ ሥልጣንና ተግባር በክልሉ ሕገመንግስት አንቀጽ ፷ ላይ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

**5. የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት**

1) ርዕሰ መስተዳድር፤
2) ምክትል ርዕሰ መስተዳድር፤
3) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት የተቋቋሙ አስፈጻሚ ተቋማት ኃላፊዎች፤
4) ርዕሰ መስተዳድሩ በአባልነት እንዲሳተፉ የሚመርጣቸው ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የሚጨመሩ አባላት በዚህ አዋጅ ከተመሰረተው ከአጠቃላይ የመስተዳድር ምክር ቤቱ አባላት ብዛት ከአንድ ሦስተኛ በላይ መሆን የለባቸውም፡፡
6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከቱ የአስፈጻሚ ተቋማት ኃላፊዎች በመስተዳድር ምክር ቤቱ ስብሰባ ለመገኘት በማይችሉበት ጊዜ በግልጽ በሚሰጥ ውክልና ምክትል ኃላፊዎች መሳተፍ ይችላሉ፡፡

**6. <u>Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Mini Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>**

Qoqqowu jeefisiisaanote amaale mini biilloonyinna loosu qeechi qoqqowu bayriidi seeri quwa 57 aana worroonni garinni ikkanno.

**7. <u>Jefisiisanote Amaale Mini Gambooshshu Amanyoote</u>**

1) Jefisiisanote amaale mini:
   (a) Loososi garunni harisate gidooyidi galtinote Wodho heedhannosi;
   (b) Gatinote wodhonni gumulannihu garinni madabanyanna wiinamu gambooshshe harisanno;
   (c) Gambooshshu aaana miillate giddonni bocu aleenni ikkitannori leelturo wo’ma songo ikkitanno;
   (d) Sayisanno gumulo halamate huuronni ikkitanno, halamate huuronni gumula dandaa hoongiro rooridi huuronni gumulanni; uynoonni huuro taalo dagguro prezidantichu noo bisi huro gumulo ikktanno.
2) Prezidantichu:
   (a) Jefisiisanote amaale mini miilla ajanda amadisiisate qoossonsa noo gedeenni heedhenna amaalete minira ajandimmate shiqqanno hajubba gumulanno;
   (b) Amaalete mini gambooshshe massaganno;
   (c) Amaalete minira ajandu garinni shiqqino hajo la’annosi komitenni la’ama hasiissanoseta ikkite leelturo gambooshshe wole yannara sayisanno.
3) Prezidantichu heeranokki yannara aantanchu prezidantichi amaalete mini gambooshshe massaganno.

6. **<u>የመስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

የመስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር በክልሉ ሕገመንግስት አንቀጽ ፶፯ ላይ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

7. **<u>የመስተዳድር ምክር ቤት የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>**

1) የመስተዳድር ምክር ቤት፤

(ሀ) ሥራውን በአግባቡ ለማካሄድ አስፈላጊው የውስጥ ደንብ ይኖረዋል፤

(ለ) በውስጠ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፤

(ሐ) ስብሰባ ላይ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤

(መ) የሚያስተላልፈው ውሳኔ በተባበረ ድምጽ ይሆናል፣ በተባበረ ድምጽ መወሰን ካልተቻለ በአብልጫ ድምጽ ይወሰናል፤ የተሰጠው ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ርዕሰ መስተዳድሩ ያለበት ወገን ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

2) ርዕሰ መስተዳድሩ፤

(ሀ) የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፤

(ለ) የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፤

(ሐ) ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የቀረበ ጉዳይ በሚመለከተው ኮሚቴ መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል፡፡

3) ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፡፡

**8. Jefisiisanote Amaale Mini Komite**

1) Jefisiisanote amaale mini biillonyenna loosu qeechasi fulate kaa'lannosi gede amaalete mini miilla afantanno addi addi komite amaalete mini gambisaanchinni uurritara dandiitanno.
2) Komitete biilloonyinna loosu qeechi amaalete mini gidooyidi galtinote wodhonni gumulanni.

## GAFA SASE

## Jeefisiisaanote Bisubba Uurro, Tantano, Biilloonyenna Loosu Qeechansa

**9. Jeefisiisaano Bissa Uurra**

Pirezidantichu hundaanonna Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Minira miilla ikkitinori konni woroonni dirroonniri jeefisiisaano bissa seeru mannimma noonsare ikkite konni lallawinni uurritino:

1) Keerunna Gal'abbote Biiro;
2) Irshunna Kalaqamu Jiro Latishshi Biiro;
3) Fayyimmate Biiro;
4) Rosu Biiro;
5) Womaashshu Biiro;
6) Farcote Biiro;
7) Eote Biilloonye;
8) Doogote Latishshinna Hodhishshu Biiro;
9) Industirete Latishshi Biiro;
10) Quchumunna Safote Latishshi Biiro;
11) Way, Shiilotenna Inerjete Biiro;

**8. የመስተዳድር ምክር ቤት ኮሚቴዎች**

1) የመስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ይረዳው ዘንድ የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች በምክር ቤቱ ሰብሳቢ አማካኝነት ሊቋቋም ይችላል፡፡
2) የኮሚቴዎች ሥልጣንና ተግባር በምክር ቤቱ ውስጠ ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የአስፈጻሚ አካላት መቋቋም፣ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባር

**9. የአስፈጻሚ አካላት መቋቋም**

ለርዕስ መስተዳድሩ ተጠሪ እና የመስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አስፈጻሚ አካላት የሕግ ሰውነት ያላቸው ሆነው በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፤

1) የሠላምና ፀጥታ ቢሮ፤
2) የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ፤
3) የጤና ቢሮ፤
4) የትምህርት ቢሮ፤
5) የገንዘብ ቢሮ፤
6) የፍትህ ቢሮ፤
7) የገቢዎች ባለሥልጣን፤
8) የመንገድ ልማትና ትራንስፖርት ቢሮ፤
9) የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ፤
10) የከተማና መሠረተ-ልማት ቢሮ፤
11) የውሃ፤ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ፤

12) Meentu, Wedellunna Dagoomitte Hajubba Biiro;
13) Wogate, Turizimetenna Ispoortete Biiro;
14) Loosunna Dandoote Biiro;
15) Dagitte Owaantenna Mannu Jiro Latishshi Biiro;
16) Kominikeeshinete Biiro;
17) Pilaanetenna Latishshi Biiro;
18) Saadate Jiro Latishshi Biiro;
19) Daddalunna Dikkote Latishshi Biiro;
20) Baattote Gashshootinna Investimentete Biiro.

**10. <u>Jefisiisano Bissa Loosu Handaari Tantano</u>**

1) Gumaamimansa ledatenna jiro garunni horonsirate jefisiisanote amaale mini gumulonni duucha jefisiisanonna hundaano jefisiisano bissa loosu handaari tantano dagitte owaantenna mannu jiro latishshi biiro widoonni mittimmatenni xiinxalinenna loosu aana hossara dandiitanno.

2) Konni quwira cinaancho quwa (1) worroonnihu noowa heerenna loosisi akati kaiminni hojji loosu tantano xiinxallo hasiisannosi jefisiisanchi woy hundaanchu jefisiisanchi bisi jefisiisanote amaale mini fajjisiro hojji loosu tantano xiinxallo harisatenni xiinxallote gumi jefisiisanote amaale minira shiqannanna gumullanna loosu aana hossinsara

12) የሴቶች፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤
13) የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ፤
14) የሥራና ክህሎት ቢሮ፤
15) የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ፤
16) የኮሚዩኒኬሽን ቢሮ፤
17) የፕላንና ልማት ቢሮ፤
18) የእንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ፤
19) የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ፤
20) የመሬት አስተዳደርና ኢንቨስትመንት ቢሮ

**10. <u>የአስፈጻሚ ተቋማት የሥራ ዘርፍ አደረጃጀት</u>**

1) ውጤታማነትን ለመጨመርና ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም ሲባል በመስተዳድር ምክር ቤት ውሳኔ የበርካታ አስፈጻሚ እና ተጠሪ አስፈጻሚ ተቋማት የሥራ ዘርፍ አደረጃጀት በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ አማካይነት በጋራ ተጠንቶ እንዲተገበር ሊደረግ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሥራው ባህሪ የተነሳ የተናጠል የሥራ አደረጃጀት ጥናት የሚያስፈልገው አስፈጻሚ ወይም ተጠሪ አስፈጻሚ ተቋም በመስተዳድር ምክር ቤቱ ሲፈቀድለት የተናጠል የሥራ አደረጃጀት ጥናት በማካሄድ የጥናት ውጤቱ ለመስተዳድር ምክር ቤት እየቀረበ እና እየተወሰነ ተግባራዊ ሊደረግ

dandiinanni.

## GAFA SHOOLE

## Biirote Biilloonyenna Loosu Qeecha

### 11. Biirote Gutu Biilloonyenna Loosu Qeecha

Konni lallawi quwa 9 garinni uurrinsoonni mitte mittenti biironna biirote deerrinni uurrinsonni jefisiisancho bisi aantete worronni gutu biilloonyinna loosu qeechi he’rannose:

1) Seeranna polise burqissanno; mixonna baajeette qixxeessitanno; fajjinirono loosu aana hosiissanno.
2) Xiinxallo ha’rissanno; dhuku kaajjishshi pirogiraamma loosu aana hosiissanno; taje gamba assitanno; qineessitanno; hasiishshu garinni tuqissanno.
3) Federaaletenna qoqqowu seeri loosu aana hosasi buuxxanno.
4) Seeru garinni sheemaatenna sumumme assitanno; loosaasine qaxartanno; gashshitanno; geegiissitanno.
5) Echi.ay.vi Eedisi eddaramaanonna bisu gawajjamaano taalo horaameeyyenna wo’ma beeqqaasine ikkitanno ikkito injeessitxanno.
6) Qixxeessitanno polisenni, seerinni, latishshu pirogiraammanninna pirojektuwanni meentunna wedellu hajo, qaaqquullu horonna hobbanke agarsiissanno; qarqaru agarooshshe, danote gargarooshshi loosi massagooshshe, mannihimmate

ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## የቢሮዎች ሥልጣን እና ተግባር

### 11. የቢሮዎች የወል ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት የተቋቋመ እያንዳንዱ ቢሮ እና በቢሮ ደራጃ የተቋቋመ አስፈጻሚ አካል ቀጥሎ የተመለከቱ የወል ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1) ሕግና ፖሊሲዎች ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣
2) ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን ተግባራዊ ያደርጋል፣መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ እንደአስፈላጊነቱ ያሰራጫል፣
3) የፌዴራልና የክልሉ ሕጎች በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
4) በሕግ መሰረት ውሎችና ስምምነቶች ያደርጋል፣ ሠራተኛ ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣
5) የኤች አይቪ ኤድስ ተጠቂዎችንና የአካል ጉዳተኞች የእኩል ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
6) በሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳይ፣ የሕጻናት ጥቅምና ደህንነትን ያስጠብቃል፣ የአካባቢ ጥበቃን፣ የአደጋ ስጋት ስራ አመራርን፣ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር መካተታቸውን

qoosso assootubba pirogiraamete giddo hanqafamase buuxxanno; loosu aana hosiissanno.

7) Qoqqowu woy federaalete mootimma fushshitino ikkadimmate buuxishshi seeri garinni hasiissanno loosu millimmo aana ikkadimma buuxxanno.
8) Hundaasine ikkitino uurrinshuwa aliidimmatenni buusansiisanno; loosu mixo, baajeettenna yannite guuntete rippoortensa qineessatenni qoqqowu jeefisiisaanote amaale minira shiqishatenni kaajjishiishanno.
9) Wole seerubbanni aamantino biilloonyenna loosu qeecha jeefissanno, jeefisiissanno.

**12. <u>Keerunna Gal’abbote Biiro</u>**

1) Dagate keerenna adawa agartanno; ha’runsitanno; buuxisiissanno; daga beeqqisiissanno.
2) Dagate ga’labbonna adawi hajo aana loossanno garimma noonsa federaalete, qoqqowunna woraddate bisubba ledo xaadooshshe kalaqqanno.
3) Qasiisote qoqqowubba ledo ka’anno kiphonna sumiimme hoonge keeraancho doogonni tirtanno; la’annonsanna qoqqowubbanna federaalete mootimma isubba ledo buusante loossanno.
4) Ga’labbote looso lainohunni qoqqowu mootimma amaaltanno.
5) Qoqqowu, hojjimmootunna gaamote mereero keeru, ayirrisamatenna mimmito duqqate budi bowiranno gede hegershunna millimmote hayyo maltanno; loosu aana hosate garano ha’runsitanno.
6) Qoqqowoho ka”annohu sumiimmete hoonginna kipho keeraancho doogonni tidhantara la’annonsa

ያረጋግጣል፣ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

7) የክልል ወይም የፌዴራል መንግስት ባወጣው የብቃት ማረጋገጫ ሕግ መሰረት በሚመለከተው የስራ እንቅስቃሴ ላይ ብቃት ያረጋግጣል፡፡
8) ተጠሪ የሆኑ ተቋማትን በበላይነት ያስተባብራል፣ የሥራ ዕቅድ፣ በጀት እና ወቅታዊ የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን በማጠናቀር ለመስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ ያጸድቃል፡፡
9) በሌሎች ሕጎች የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፡፡

**12. <u>የሠላምና ፀጥታ ቢሮ</u>**

1) የህዝብ ሠላምና ደህንነት ይጠብቃል፣ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ህዝብ ያሳትፋል፡፡
2) በህዝብ ፀጥታና ደህንነት ጉዳይ ከሚሰሩ አግባብነት ካላቸው ከፌደራል፣ ክልሎች እና ወረዳዎች አካላትጋር ግንኙነት ይመሰርታል፡፡
3) ከአጎራባች ክልሎች ጋር የሚነሱ ግጭቶችና አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ ይፈታል፣ ከሚመለከታቸው ክልሎችና የፌደራል መንግስት አካላት ጋር ተባብሮ ይሰራል፡፡
4) የፀጥታ ሥራን በሚመለከት የክልሉን መንግስት ያማክራል፡፡
5) በክልሉ በግለሰቦችና በቡድኖች መካከል የሰላም፣ የመከባበርና የመቻቻል ባህል እንዲዳብር የግንዛቤና ንቅናቄ ስልቶችን ይቀይሳል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፡፡
6) በክልሉ የሚነሱ አለመግባባቶችና ግጭቶች

bisubba ledo waacante loossanno.

7) Qoqqowu giddo yannillaancho ikkitino mashalaqqete lolanke amadooshshinna qinaawo heedhanno gede hayyo maltanno; loosu aana hosiissanno.

8) Ga’labote mashalaqqe gamba assatenna gashshate kaa’litannota addita womaashshunna baajeettete gashshootinna mannu wolqa gashshooti wodho qoqqowu mootimma amaale mini muronni loosu aana hosiissanno.

9) Qoqqowunniha ga’labbote gara lainohunni halamaano bisubba ledo buusamatenni kiphote kori aana xiinxallo ha’rissanno; furgaote hedonna gumulsiisaano hayyo shiqishshanno; fajjinanni woyteno loosu aana hosiissanno.

10) Qoqqowu giddo millissannore amma’notenna ammanote uurrinshuwa borreessite amadanno; tajete woraqata uytanno; ha’runsitanno; fajjoote haaroonsitanno; seeriweelo fajjoote ikkite leeltannore ittissanno; hooltanno.

11) Ga’labbote booraambe woy kalaqamu dano kalaqanturo adhinanni gargarooshshu qaafora gimarootunna qaaqquullu aana gawajjo iillitannokki gede qorophote qaafo adhitanno.

12) Milishu wolqa ga’labbo ayirrisiisate dandiissanno garinni qiaawatenni dagatenna wole ga’labbote wolqa ledo waaxame loosanno gara injeessitanno.

13) Milishu wolqa seeda yanna qaru loosinsanni baxxitukkinni ga’labbotenna wolu mootimmate

በሠላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፡፡

7) በክልሉ ውስጥ ዘመናዊ የሆነ የፀጥታ መረጃ ፍሰት አያያዝና አደረጃጀት እንዲኖር ስልት ይቀይሳል፣ ይተነትናል፣ ይተገብራል፡፡

8) የፀጥታ መረጃ ለማሰባሰብና ለማስተዳደር የሚረዳ ልዩ የፋይናንስና የበጀት አስተዳደር እንዲሁም የሰው ኃይል አስተዳደር ደንብ በመስተዳድር ምክር ቤት ውሳኔ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡.

9) የክልሉን የፀጥታ ሁኔታን በሚመለከት ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር በግጭት መነሻ ምክንያቶች ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ የመፍትሔ ሃሳቦችና የአፈፃፀም ስትራቴጂዎችን ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

10) በክልሉ ውስጥ የሚንቀሣቀሱ የሃይማኖትና የእምነት ተቋማትን ይመዘግባል፣ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ ፈቃድ ያድሣል፣ ሕገ-ወጥ ሆነው ሲገኙ ፈቃድ ያግዳል፣ ይሰርዛል፡፡

11) የፀጥታ መደፍረስ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት በሚወሰደው የመከላከል እርምጃ በሴቶችና በህፃናት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የጥንቃቄ እርምጃ ይወስዳል፡፡

12) የሚሊሻ ኃይል ፀጥታን ለማስከበር በሚያስችል አኳኋን በማደራጀት ከህዝቡና ከሌሎች የፀጥታ ኃይሎች ጋር በቅንጅት የሚሰራበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

13) የሚሊሻ ኃይል ለረጅም ጊዜ ከምርት ሥራው ሳይነጠል በፀጥታና በሌሎች መንግሥታዊ

loosira bobbakkanno gede assitanno; dhuku kaajjishshi qajeelsha afi'rannno gede assitanno.

14) Milishu wolqara hasiissanno qodhonna udiinni kaajjannonna wo'mano gede assitanno; tittirshu wodhotenni muramanno.

15) Biirote loosaasine loosinsa qansichootunnita bayriidi seeri qoosso gurchitannokki doogonni wo'manno gede assitanno.

16) Hexxo wonshiishate kaa'lannoha wole assooteno loossanno.

**13. Irshunna Kalaqamu Jiro Latishshi Biiro**

1) Qoqqowunnita irshunna kalaqamu jiro, irshu laalchonna eote dikki'ro, irshu eo shiqisho lainohunni polisete hedo shiqishshanno; qixxeessitanno; gumulsiishshu aanti-gedeni istiraateeje fushshitanno; kaajjirono loosu aana hosiissanno.

2) Baadiyyete sagalete waastinni qarrira reqeccishantino qarqarranna dagoomu biso badanno; kora xiinxallanno; irkisanno; sagalete waastinni pirogiraamma massagganno; handaaraho loossannore qeechi-gutamaano bisubba buusansiissanno.

3) Baatto loosidhe galtinorira aamantannota irshunna kalaqamu jiro ekisteenshiinete owaante hala'litara loossanno; jawaachishshanno.

4) Garimma noonsa bisubba ledo buusamatenni baatto loosidhe galtinori irshunna kalaqamu jiro loosonsa woyyeesi'rate hasiissannonsata liqoote injo afidhanno gara injeessitano.

ሥራዎች ላይ እንዲሰማራ ያደርጋል፣ የአቅም ግንባታ ሥልጠና እንዲያገኝ ያደርጋል።

14) ለሚሊሻ ኃይል የሚያስፈልግ ትጥቅና አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች እንዲጠናከርና እንዲሟላ ያደርጋል፣ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል።

15) የቢሮው ሠራተኞች ስራቸው የዜጎችን ህገመንግስታዊ መብት በማይፃረር መንገድ እንዲፈፅሙ ያደርጋል።

16) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

**13. የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ**

1) የክልሉን የእርሻና፣ የተፈጥሮ ሃብት፣ የእርሻ ምርትና ግብዓት ግብይት፣ የእርሻ ግብዓት አቅርቦትን በሚመለከት የፖሊሲ ሃሳቦችን ያቀርባል፣ ያዘጋጃል፣ የአፈፃፀም ቅደም ተከተል ስትራቴጂ ያወጣል፣ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡

2) በገጠር ለምግብ ዋስትና ችግር የተጋለጡ አካባቢዎችንና የኅብረተሰብ ክፍሎችን ይለያል፣ መንስኤውን ያጠናል፣ ይደግፋል፣ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች ይመራል፣ በዘርፉ የሚሠሩ ባለድርሻ አካላትን ያስተባብራል።

3) ለአርሶ አደሩ የሚሰጡ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ይሰራል፣ ያበረታታል።

4) አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር አርሶ አደሩ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሥራውን ለማሻሻል የሚያስፈልገውን የብድር አቅርቦት የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

5) Irshu latishshi aana hekko kalaqara dandaannore ha’runsitanno; balxiqorophotenna balaxiqixaawote amuraate diriirsitanno.

6) Qoqqowoho daafotenna taraawanno gidu dhibbanna gidimale gargaratenna qorqorate hasiissanno qaafo adhitanno.

7) Gorsu latishshi loosi hala’lanno gede jeefisiisate hayyo qixxeessitanno; hajo la’’anno bissa ledo loossanno.

8) Qoqqowoho hala’litanno paakeejuwa loosu aana hosiisate hasiissannota irshu eora ikkitannorenna liqoo hasi’nanni silanchimmanni, bikkinninna yannanni baatto loosidhe galtinorira shiqishshanno; irshu laalchi baadinna baara widi dikko safo assi’rinoha ikkanno gede injeessitanno; ha’runsitanno; illaallissanno.

9) Irshu laalchimma lossate kaa’litanno xiinxallo ha’rinsanni gede assitanno; loosu aana hosansa ha’runsitanno.

10) Qoqqowunniti kalaqamu jiro lattanno gede, qorowantanno gedenna horoonshise woyyaawanno gede irkissanno polisenna istiraateeje qixxeessitanno; kaajjituro loosu aana hosiissanno; loosu aana hosansa garan ha’runsitanno; illaallissanno.

11) Giwirinnu xiinxallo qeechigutamaano bisubba waaxantenna buusante loossanno amuraate diriirsitanno.

12) Meentonna wedella safo assidhinota irshunna kalaqamu jiro paakeeje polisete deerrinni qixxeessitanno; kaajjituro loosu aana hosanna gara

5) በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ይከታተላል፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያና ቅድመ ዝግጁነት ስርዓት ይዘረጋል።

6) በክልሉ የወረረሽኝና ተዛማች አዝርዕት በሽታዎችና ፀረሰብል ለመከላከልና ለመቆጣጠር አስፈላጊ እርምጃ ይወስዳል።

7) የመስኖ ልማት ስራ እንዲስፋፋ የአፈፃፀም ስልቶችን ያዘጋጃል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር ይሰራል።

8) በክልሉ የሚስፋፉ ፓኬጆች ለመተግበር የሚያስፈልጉ የእርሻ ግብአቶችና ብድሮች በሚፈለገው ጥራት፣ መጠንና ጊዜ ለአርሶ አደሩ ያቀርባል፤ የእርሻ ምርት የውስጥና ውጪ አገር ገበያ መሰረት ያደረገ እንዲሆን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

9) የእርሻ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዱ ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል።

10) የክልሉ የተፈጥሮ ሃብት እንዲለማ፣ እንዲታቀብና አጠቃቀሙ እንዲሻሻል የሚያግዝ ፖሊሲና ስትራተጂ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅ በተግባር ያውላል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

11) የግብርና ምርምር ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና በትብብር የሚሰሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል።

12) ሴቶችና ወጣቶችን መሰረት ያደረጉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ፓኬጅ በፖሊሲ ደረጃ ይቀርፃል፣ ሲፀድቁ ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

ha’runsitanno.

13) Dikko shiqqannore eo ikkitanno bushshu shiilonna irshu guma labbinori isilanchimma buuxxanno; ha’runsitanno; illaallissanno.

14) Kalaqamu Ofollanni luphi yitino bagaame woy babbaxino kmorkaatinni mulqantinonna haqqe noikki baatto adaramino dubbinni su’mitanno, gashshitanno.

15) Laalcho uyitannonna agaramino dubbo federaale fushshitanno safarancho garinni baddanno, su’mitanno, dubbu latishshi paakeeje federaalete istaandarde kaiminni qixxeessitanno, loosu aana hosiissanno.

16) Dubbu latishshira ikkitanno kaashsho qixxeessatenni kayiinsara biddi assitanno, irkissanno, gumaamimma buuxxanno, harunsitanno, dubbu amado base hajo la’’annohu ledo halamatenni amadote annimma taje uyinara assitanno

17) Irshunna kalaqamu jiro latishsha lainohunni giwirinnu xiinxallo inistitiyutenni loosantanno xiinxawo aliidimatenni massaganno;

18) Hexxo jeefo gansiissannota wole assootubbano loossanno.

**14. <u>Fayyimmate Biiro</u>**

1) Qoqqowoho fayyimmanna fayyimmate ledo xaaddanno hajubba aliidimmatenni massagganno; buusansiissanno;

2) Fayyimmate owaante tuqisaanchimma lophitanno gede hasiissanno jawaante assitanno;

3) Liiqotenninna kaa’lotenni wo’mitannota fayyimmate

13) ወደ ገበያ የሚቀርቡ ግብአቶች እንደ ማዳበሪያና የእርሻ ውጤቶች ጥራት ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

14) በተፈጥሮ አቀማመጡ ከፍተኛ ተዳፈታማ የሆኑ ወይንም በተለያዩ ምክንያቶች የተራቆቱ እና ዛፍ የሌላቸው መሬቶችን በጥብቅ ደንነት በመሰየም፤ ያስተዳድራል፡፡

15) ምርት ሰጪ እና ጥብቅ ደኖችን በፌደራል በሚወጣው መመዘኛ መስፈርት መሰረት ይለያል፤ይሰይማል፤የደን ልማት ፓኬጆችን በፌደራል ስታንዳርድ መሰረት ያዘጋጃል፤ስራ ላይ ያውላል፡፡

16) ለደን ልማት የሚውሉ ችግኞችን በማዘጋጀት እንዲተከሉ ያደርጋል፤ ይደግፋል፤ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፤ የደን ዞታ ቦታዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የደን ባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖራቸው ያደርጋል፤

17) የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት በተመለከተ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሚከናወኑ ምርምሮችን በበላይነት ይመራል፤

18) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**14. <u>የጤና ቢሮ</u>**

1) በክልሉ ጤናና ጤና ነክ ጉዳዮችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡

2) የጤና አገልግሎት ሽፋን እንዲያድግ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፡፡

3) በብድርና ዕርዳታ የሚከናወኑ የጤና

pirogiraamma gumulaanchimma ha'runsitanno; buusansiissanno;

4) Fayyimmate handaari latishshita qoqqowaancho pirogiraame qixxeessitanno; gumulaanchimmase ha'runsitanno; keentanno;

5) Qoqqowaancho fayyimmate mashalaqqe amuraate massagganno; buusansiissanno; gumulaanchimmase ha'runsitanno;

6) Daafonna taraawanno dhibba gargarate dandiissitanno hayyo maltanno; loosu aana hossanno gara ha'runsitanno;

7) Qoqqowaancho saga'late amuraati istiraateeje jeefishsha ha'runsitanno; buusansiissanno;

8) Dagoomu fayyimma qohara dandaannori kalaqamiro gargarooshshu qaafo adhitanno; buusansiissanno;

9) Qoqqowu giddo hasiisaano xagganaa xagishshu udiinni ikkadu garinni hee'ransanna garunni horote hosansa buuxxanno;

10) Qoqqowoho afantannore mootimmate fayyiimate uurrinshuwa xintitanno; gashshanno;

11) Fayyimmate amuraati kaarta qixxeessitanno; fayyimmannihu safote latishshi hala'lanno gede assitanno; irkono uytanno;

12) Qoqqowoho echi.ay.vii eedisi gargarate, illaallisatenna baci-tuqu assoote aliidimmatenni

ፕሮግራሞችን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፡፡

4) የጤናውን ዘርፍ ልማት ክልላዊ ፕሮግራም ይነድፋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፡፡

5) ክልላዊ የጤና መረጃ ሥርዓቱን ይመራል፣ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

6) ወረርሽኝና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፡፡

7) ክልላዊ የአመጋገብ ሥርዓት ስትራቴጂን አፈጻፀም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፡፡

8) የሕብረተሰቡን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የመከላከል እርምጃ ይወስዳል ያስተባብራል፡፡

9) በክልሉ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መድሐኒቶችና የሕክምና መሳሪያዎች በበቂ መጠን መኖራቸውንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡

10) በክልሉ የሚገኙ የመንግስት ጤና ተቋማትን ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፡፡

11) የጤና ሥርዓቱን ካርታ ያዘጋጃል፣ የጤና መሰረተ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ድጋፍም ይሰጣል፡፡

12) በክልሉ ኤች አይቪ ኤድስን የመከላከል፣ የመቆጣጠርና የዘርፈ ብዙ ምላሽ ተግባርን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣

massagganno; buusansiissanno; ha’runsitanno; illaallissanno;

13) Qoqqowunniha fayyimmate qarra tiratenna fayyimmate owaante aa gara woyyeessate kaa’litanno xiinxallo ha’risantanno gede hasiissanno irko assitanno;
14) Garimma noonsare addi addi hayyo horoonsi’ratenni fayyimma agadhate rosi hala’lanno gede assitanno;
15) Qoqqowoho fayyimmate rosinna qajeelshi uurrinshuwa uurrissanno; qineessitanno; gashshitanno;
16) Qoqqowoho sagalete, xagichunna fayyimmate qorowooshshi gashshootinna qorqorshu loossa garunni jeefamansa buuxanno;
17) Hursaanchimmansa buuxantinore baadi xagganna xagishshu hayyo dagate owaantera hossanno gede xiinxallo assitanno; loosu aana hosansa garira millissanno;
18) Daga fayyimmase hajo annimma aana muraancho ikkanno gede saga’late, qarqaru co’immara, bikkancho ilara, amuwunna qaaqquullu qorowora lowo illacha tugge millissanno; akatu soorro buuxisiisanno fayyimma agadhate roso uytanno;
19) Hexxo jeefo gansiisate kaa’litannota wole assootubba loossanno.

**15. <u>Rosu Biiro</u>**

1) Rosanna rosiisate looso aliidimmatenni massagganno;
2) Qoqqowu rosinna qajeelshi deerrasinna silanchimmasi agadhinoha ikkasi buuxxanno; hasiissanno qaafo adhitanno; maxaaffanna rosu

ይቆጣጠራል፡፡

13) የክልሉን የጤና ችግር ለመፍታትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚረዱ ምርምሮች እንዲካሄዱ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡
14) አግባብነት ያላቸው የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የጤና አጠባበቅ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡
15) በክልሉ የጤና ትምህርትና ስልጠና ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፡፡
16) በክልሉ የምግብ፣ የመድሐኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፡፡
17) ፈዋሽነታቸው የተረጋገጠ ባህላዊ መድሓኒቶችና የህክምና ዘዴዎች ለህዝብ አገልግሎት እንዲውሉ ጥናት ያካሂዳል፣ ለተግባራዊነቱ ይንቀሳቀሳል፡፡
18) ሕዝቡ የጤናው ጉዳይ ባለቤትና ወሳኝ እንዲሆን በአመጋገብ፣ ከባቢያዊ ፅዳት፣ የወሊድ ምጣኔ፣ የእናቶችና ህፃናት እንክብካቤ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል፣ ባህሪያዊ ለውጥ የሚያረጋግጥ ብቁ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ይሰጣል፡፡
19) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**15. <u>የትምህርት ቢሮ</u>**

1) የመማር ማስተማር ሥራን በበላይነት ይመራል፡፡
2) የክልሉ ትምህርትና ሥልጠና ደረጃውንና ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣ መጽሐፍትንና የትምህርት

kaa’looshshi udiinne wonshitanno; tuqissanno;

3) Rosiisaanote beehooshshenna gaamishsha ha’rissanno; deerru deerunkunni rosiisate ikkado assannori wo’masi buuxxanno; rosiisaanote qajeelsha uytanno;
4) Umi dirimi rosiha jeefote fonqolo qixxeessitanno; jeefisamasi gara massagganno; tajete woraqata uytanno;
5) Gobboomu deerrinni qixxaawino fonqolo qoqqowoho wonshiishshanno;
6) Qoqqowoho dirinsa rosoho iillino qaaqquullenna wedella rosate kaayyo afidhanno doogo injeessitanno; loosu aana hosiissanno;
7) Uminna layinki dirimi rosita rosu maxaaffa attamonna tuqishsha ha’rissanno; ha’ranno gede assitanno;
8) Mootimmaaano, mootimmaaweelo uurrinshuwanna annanni rosi minnaha ikkadimmate deerra buuxxanno; fajjoote uytanno; uynoonni fajjoote hoolanno;
9) Rosu uurrinshuwaha gumulsiisate dhuki qarra baddanno; mixo qixxeessatenni qarraho tiro uytanno;
10) Rosiisaanonnihanna rosu massagaano bisubbaha gumulsiisate dhuka kaajjishshanno;
11) Balaxote, addi hasatto, jajjabbunna doorshunniha safote rosi xintamooshshe murtanno; pirogiraame fushshitanno; ha’runsitanno; irko assitanno;

መርጃ መሣሪያዎችን ያሟላል፣ ያሠራጫል፡፡

3) የመምህራን ድልድልና ምደባ ያካሂዳል፣ በየደረጃው ለማስተማር ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ ለመምህራን ስልጠና ይሰጣል፡፡
4) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ያስተዳድራል፣ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
5) በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጁ ፈተናዎችን በክልሉ ያስፈጽማል፡፡
6) በክልሉ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናትና ወጣቶች የመማር ዕድል የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
7) የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍት ህትመትና ስርጭት ያከናውናል፣ እንዲከናወን ያደርጋል፡፡
8) የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ትምህርት ቤቶችን የብቃት ደረጃ ያረጋግጣል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይሰርዛል፡፡
9) የትምህርት ተቋማትን የማስፈፀም አቅም ችግሮችን ይለያል፣ ዕቅድ በመንደፍ ለችግሮቹ መፍትሔ ይሰጣል፡፡
10) የመምህራንና የትምህርት አመራር አካላት የመፈፀም አቅም ይገነባል፡፡
11) የቅድመ መደበኛ፣ የልዩ ፍላጐት፣ የጐልማሶችና የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርቶችን አደረጃጀት ይወስናል፣ መርሃ ግብር ያወጣል ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

12) Rosu gumaamimma lossate madabanyu rosira balaxxote rosi pirogiraame qixxeessitanno, jeefishsha massaganno;
13) Rosanna rosiisate keeno aate qarranna guuntete aana xiinxallo ha'rissanno; tirote raga maltanno; hasiissanno qaafo adhitanno;
14) Umi dirimi Rosi kaarkuleeme qixxeessitanno; qoqqowoho loosu aana hosiissanno;
15) Hexxo jeefa gansiissannota wole assootubbano loossanno.

**16. <u>Womaashshu Biiro</u>**

1) Qoqqowu mootimma baajete qixxeessitanno, fajjinonni baajete kaiminni baattanno, baajetete jeefishsha gashshitanno, keentanno, qorqortanno;
2) Qoqqowu mootimma baajeette, shallago, baatooshshe, giddoydi odiite amanyoote xintitanno, loosu aana hosase ha'runsitanno;
3) Mootimmaanonna mootimmaaweelo uurrinshuwanni afantanno kaa'lonna liqoo buusansiisatenni qoqqowu latishshu baajeette mixo ledo qinaawe loosu aana hossara injeessitanno; qineessitanno; ha'runsitanno.
4) Qoqqowoho leeltannota dagoomaanchonna miinjitte mitiimma shotisate sumiimmete kaiminni dagganno kaa'lo loosu aana hossara irko assitanno; buusansiissanno; gashshitanno; lexxote kaa'lo afi'rate

12) የትምህርት ውጤታማነት ለማሳደግ የቅድመ-መደበኛ መርሃ ግብር ይቀርፃል፤ አፈፃፀሙን ይመራል፤
13) የመማር ማስተማር ምዘና አሰጣጥ ችግሮችና ውጤታማነት ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ይቀይሳል፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
14) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርትን ያዘጋጃል፣ በክልሉ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
15) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**16. <u>የገንዘብ ቢሮ</u>**

1) የክልል መንግሥት በጀት ያዘጋጃል፣ በተፈቀደው በጀት መሰረት ክፍያ ይፈፅማል፣ የበጀቱን አፈፃፀም ያስተዳድራል፣ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፡፡
2) የክልሉ መንግስትን የበጀት፣ የሂሳብ፣ የክፍያና፣ የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፣ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡
3) ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝ እርዳታና ብድር በማስተባበር ከክልሉ የልማት በጀት ዕቅድ ተጣጥሞ በስራ እንዲውል ያመቻቻል፣ ያቀናጃል፣ ይከታተላል፡፡
4) በክልሉ የሚታዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለማቃለል በስምምነት መሰረት የሚመጡ እርዳታዎች በስራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ ያስተዳድራል፣ ተጨማሪ እርዳታዎች ለማግኘች የተለያዩ

babbaxxitino pirojektuwa qixxeessatenninna qixxeessiisatenni kaa’lo assitanno uurrinshuwara shiqishshanno;

5) Miinjunna dagoomu latishshi handaarira bobbakkinore mootimmaanonna mootimmaaweelo uurrinshuwa looso la’annonsari ledo halamatenni buusansiissanno; illaallissanno;
6) Fajjaameeyye uurrinshuwanna maammarra pirogiraammatanna pirojektuwata ikkadimmate keeno assitanno; loosu sheemaate malaatisantanno; buusansiissanno; ha’runsitanno; keentanno.
7) Qoqqowunniti mootimmate bisubba qoqqowu mootimma womaashshu polisenna seeri garinni loosansa illaallissanno;
8) Qoqqowu mootimmaha eo gamba assinanni woraqata attansiissanno; tuqissanno; ha’runsitanno; qorqortanno;
9) Qoqqowu mootimma fiisikaaletenna womaashshu loosi guunte leellishannoha tittirshu xawishsha pirezidaantichaho, qoqqowu jeefisiisaanote amaale miniranna seerunni biilloonye uynoonninsa bisubbara yannatenni shiqishshanno;
10) Qoqqowu mootimma shalagote amadooshshi amuraate qixxeessitanno; loosu aana hosanna gede irkissanno; giddo qorqorshi amuraate diriirsitanno;
11) Qoqqowu mootimma babbaxxitino buenni afidhannota liqootenna kaa’lote sumiimme qoqqowu mootimma su’minni malaatissanno; liqoote

ፕሮጀክቶች በመቅረፅና እንዲቀረፅ በማድረግ እርዳታ ለሚሰጡ ድርጅቶች ያቀርባል።

5) በኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዘርፍ የተሰማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ስራ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል።
6) የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን የብቃት ምዘና ያደርጋል፤ የሥራ ውል ይፈራረማል፤ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ ይገመግማል።
7) የክልሉ የመንግስት አካላት በክልሉ መንግስት የፋይናንስ ፖሊሲና ሕጎች መሰረትመስራታቸውን ይቆጣጠራል።
8) የክልሉን መንግስት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ያሳትማል፣ ያሰራጫል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
9) የክልሉ መንግስት የፋይናንስ የስራ አፈፃፀም የሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ ለርዕሰ መስተዳድሩ፣ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና በሕግ ስልጣን ለተሰጣቸው አካላት በወቅቱ ያቀርባል።
10) የክልሉ መንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ይነድፋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ይደግፋል የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል።
11) የክልሉ መንግስት ከተለያየ ምንጭ የሚያገኘውን የብድርና ዕርዳታ ስምምነት በክልሉ መንግስት ስም ይፈርማል፣ ብድሩን ያስተዳድራል።

massagooshshe gashshanno;

12) Qoqqowu mootimma aksiyonna tareessantannonna tareessantannokkiti woxu sanadda amaddanno; agartanno;

13) Qoqqowu mootimmaha jajju gashshootenna hidhote amuraate diriirsitanno; gumulaanchimma illaallissanno; irkissanno; seeraancho taashshote qaafo adhitanno; adhinanni gedeno assitanno;

14) Gongo’maasine, jajjabba maashinna, jajjabba hiro-hidho kamalte hirtanno; kayissanno; kaysate ledo amadantino loossa wonshitanno; hasiisi garinni riqiwooshshe uytanno;

15) Mootimmate hiro-hidhora ayirritanno lawashshimma leellishshanno shiqishaanora qorophishsha uytanno; murantinonna murantinokki yanna geeshsha shiqishaanchimmatenni ittissanno;

16) Qoqqowu eote wolqa lainohunni hajo la’annosi bisi ledo ikkatenni xiinxallo harissanno, hajo la’annosi bisira shiqanno gede assitanno, harunsitanno;

17) Gumulantino hidho lallawunna biddissu garinni gumulamansanna gara ikkinohu jajju gashsho amuraati diriirsamasi buuxi’rate hidhotenna jajju gashshooti qorqorsha assitanno;

18) Jeefisiisaano bisubba mootimmaano interprayzenni dhaaddo hidho gumultara fajjitanno;

19) Mootimmate gongo’maasine amadooshshinna horoonshi amuraate ha’runsinoha ikkanno gede assitanno;

20) Hexxo jeefa gansiisate kaa’litannota wole assootubba.

12) የክልሉ መንግስት አክሲዮኖች፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችና ሌሎች ተመሳሳይ የገንዘብ ሰነዶች ይይዛል፣ ይጠብቃል፡፡

13) የክልሉ መንግስት የንብረት አስተዳደር እና የግዢ ስርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፣ ይደግፋል፣ህጋዊ ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

14) ተሽከርካሪዎች፣ ትላልቅ ማሽኖች፣ ትላልቅ ግዥዎች በጥቅል ይገዛል፣ ያስወግዳል፣ ከማስወገድ ጋር የተያያዙ ስራዎች ይፈፅማል፣ እንደአስፈላጊነቱ ውክልና ይሰጣል፡፡

15) በመንግስት ግዥ አፈፃፀም ከባድ ቸልተኝነት የሚያሳዩ አቅራቢዎች ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣ ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ ከአቅራቢነት ያግዳል፡፡

16) የክልሉን የገቢ አቅም በተመለተ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ጥናት ያካሂዳል፤ ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

17) የሚፈፀሙ ግዥዎች በአዋጅና መመሪያ መሰረት መፈፀማቸውንና ትክክለኛ የንብረት አስተዳደር ስርዓት መዘርጋቱን ለማረጋገጥ የግዥና የንብረት አስተዳደር ኦዲት ያደርጋል፡፡

18) አስፈፃሚ አካላት ከመንግሥታዊ ኢንተርፕራይዝ በቀጥታ ግዥ እንዲፈፀሙ ይፈቅዳል፡፡

19) የመንግሥት ተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት የተከተለ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

20) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**17. Farcote Biiro**

Tenne jeefisiisaancho uurrinsha hojji biilloonyinna loosu qeechi lallawu kiiro 6/2012 aana worroonni garinni ikkanno.

**18. Eote Biilloonye**

1) Qoqqowunniha taksenna eo gamba assate amuraate aliidimmatenni massagganno; gashshitanno;
2) Taksete amuraate woyyeessate pirogiraame guunte annimmatenni massagganno; buusansiissanno;
3) Lifinxe, xawadimmanna xa'mamaanchimma wo'mitinohu owaante aate amuraate diriirsitanno.
4) Taksete baataanchira doorshunni takse baantanni xintamooshshe injeessanno;
5) Taksete baataano fajjootinsanni takse baattanno budi bowiranno gede hegerre kalaqate pirogiraamma loosu aana hosiissanno.
6) Qoqqowu miinju millimmo aana rumuxxitino xiinxallo ha'risatenni qoqqowunnita eote safo halashshitanno; taksete gashshootinni kalaqantanno mitiimma tidhantanno gede assitanno.
7) Taksete seera gumulsiisate hasiissannore aye manchi angano hee'ra dandiitanno sanadda la'e keentanno; amaddanno.
8) Takse murate hasiissanno mashalaqqe gamba assitanno; kaajjishshanno; kuri horoonsi'ratenni takse murtanno; gamba assitanno.
9) Taksiweelo quchumu dargi micco, minu annimma, jajjunna owaantete baatooshshi muraatishshiranna

**17. የፍትህ ቢሮ**

የዚህ አስፈጻሚ ተቋም የተናጠል ሥልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር ፮/፳፻፲፪ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

**18. የገቢዎች ባለሥልጣን**

1) የክልሉን የታክስና የገቢ አሰባሰብ ስርዓት በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2) የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አፈጻጸም በባለቤትነት ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡
3) ቀልጣፋ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
4) ለታክስ ከፋዩ አማራጭ የታክስ መክፈያ አደረጃጀቶችን ያመቻቻል፡፡
5) ታክስ ከፋዮች በፍቃደኝነት ታክስ የመክፈል ባህልን እንዲያዳብሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
6) በክልሉ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ተመስርቶ ጥናቶችን በማካሄድ የክልሉን የገቢ መሠረት ያሰፋል፣ በታክስ አስተዳደሩ የሚከሰቱ ችግሮች እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡
7) የታክስ ሕጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ሰው እጅ የሚገቡ ሰነዶችን ይመረምራል፣ ይይዛል፡፡
8) ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያጠናክራል፣ እነዚህኑ በመጠቀም ታክስ ይወስናል፣ ይሰበስባል፡፡
9) ታክስ ያልሆኑ የከተማ ቦታ ይዞታ፣ የቤት ባለቤትነት፣ የንብረትና የአገልግሎት ክፍያ

gambassiishshira kaa’litanno mashalaqquwa gamba assitanno; fatiltanno; horote hosanna gede assitanno.

10) Quchummate maazzagaajju mini eo muraatishshinna gambassiishshi xiinxallo assitanno; kamalaancho maazzagaajju mini eo gamba assinanni seeri hanqafaasincho qixxeessitanno; loosu aana hosiissanno.

11) Addi addi eo seeru garinni gamba assitanno; mootimmate gimjaabeetira eo assitanno.

12) Hexxo jeefo gansiisate kaa’lannoha wole assootubba assitanno.

**19. <u>Doogote Latishshinna Hodhdhishshu Biiro</u>**

1) Qoqqowunniha doogote latishshi looso aliidimmatenni massagganno; deerra murtanno; gashshitanno; diizaynetenna gimbaatu qorqorshi looso ha’rissanno; ha’runsitanno; illaallissanno.

2) Dagate beeqqonninna qoqqowu mootimma baajeettenni loosantannonna gatamarantanno doogo mixidhanno; tekinikete irko assitanno; looso buusansiissanno; aliidimmatenni massagganno.

3) Kalaqamu manchi woy seeru mannimma aamantino uurrinsha addi woy gutu hexxo owaantera loossino, gatamartannonna gashshitanno doogora loosu fajjoote uytanno; borreesse maareekkanno.

4) Qoqqowoho rosantinonna rosantinokkiti hodhishshu owaante hala’litanno gede assitanno.

አወሳሰንና አሰባሰብ የሚያገለግሉ መረጃዎችንይሰበስባል፣ይተነትናል፣ጥ ቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

10) የከተሞች ማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ጥናት ያደርጋል፣ የተጠቃለለ የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ የሚሰበሰብበትን የሕግ ማዕቀፍ ያዘጋጃ፣ ሥራ ላይ ያውላል፡፡

11) ገቢዎችን በሕጉ መሠረት ይሰበስባል፣ ለመንግስት ግምጃ ቤት ገቢ ያደርጋል፡፡

12) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**19. <u>የመንገድ ልማትና ትራንስፖርት ቢሮ</u>**

1) የክልሉን የመንገድ ልማት ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ደረጃ ይወስናል፣ ያስተዳድራል፣ የዲዛይንና የግንባታ ጥራትቁጥጥር ስራዎችን ያካሂዳል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

2) በህብረተሰቡ ተሳትፎ እና በክልሉ መንግስት በጀት የሚሰራና የሚጠገን መንገድ ያቅዳል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣ ስራውን ያስተባብራል፣ በበላይነት ይመራል፡፡

3) የተፈጥሮ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ለተለየ ወይም ለጋራ ዓላማ አገልግሎት ያሰራው፣ የሚጠግነው እና የሚያስተዳድረውን መንገድ የስራ ፍቃድ ይሰጣል፣ ይመዘግባል፡፡

4) በክልሉ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የትራንስፖርት አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡

5) Hodhishshu owaante shiqisho qinaabbino doogonni wo’mitaranna qoqqowunniti latishshu istiraateeje wo’millunni gumulantara lifixamase buuxxanno.
6) Hodhishshu owaante amansiissannonna adawise agaraminoha ikkasi buuxate dandiissiisannohu qorqorshu amuraati diriirsamanno gedenna loosoho hosanna gede assitanno.
7) Gobboomu hodhishshu polise garinni qoqqowoho afantanno way bisubba aana hodhishshu owaante hala’litara jawaachishshanno; fajjoote uytanno; haaroonsitanno; hooltanno.
8) Qoqqowoho hodhishshunniti safote latishshi owaante hala’litanno, woyyitannonna gatamarantanno gede assitanno.
9) Quchumaho taaksete owaantera bobbakkino hojjimmootiranna uurrinshuwara fajjoote uytanno; hakko handaarinni uurritanno maamarra borreessitanno; bobbahishsha uytanno.
10) Qoqqowoho uurinsanni gongo’maasinete gatamarshi garaazhera, gongo’mishaanote woy oofaanote qajeelshi uurinshuwaranna gongo’maasinete diru tekinikete fonqolshi uurrinshuwara fajjoote uytanno; illaallissanno; hooltanno.
11) Dagatenna hogowu gongo’maasine loosira bobbakkino bisubbara ikkadimmatenna ogimmate fajjoote uytanno; haaroonsitanno; hooltanno; uytanno owaantera baatisiissanno taariife fushshitanno; ha’runsitanno; dagate gongo’maasinera deerra fushshitanno; haaroonsitanno.

5) የትራንስፖርት አገልግሎቶች አቅርቦት በተቀናጀ መንገድ እንዲፈፀምና የክልሉን የልማት ስትራቴጂዎች በተሟላ ሁኔታ ለመፈጸም የሚያሳልጥመሆኑንያረጋግጣል፡፡
6) የትራንስፖርት አገልግሎቶች አስተማማኝና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረጋና ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
7) በሀገሪቱን የትራንስፖርት ፖሊሲዎች መሰረት በክልሉ በሚገኙ ውሃ አካላት ላይ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ይሰርዛል፡፡
8) በክልሉ የትራንስፖርት መሰረተ-ልማት አገልግሎት እንዲስፋፋ፣ እንዲሻሻልና እንዲጠገን ያደርጋል፡፡
9) በከተማ ታክሲ አገልግሎት ለሚሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ በዘርፉ የሚቋቋሙ ማህበራትን ይመዘግባል፣ ስምሪት ይሰጣል፡፡
10) በክልሉ ለሚቋቋሙ የተሽከርካሪ ጥገና ጋራዦች፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማትና ለተሽከርካሪ አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፡፡
11) በህዝብና በጭነት ማመላለሻ ሥራ ላይ ለሚሰማሩ አካላት የብቃትና የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤ ለሚሰጡት አገልግሎት የሚያስከፍሉትን ታሪፍ ያወጣል፣ ይከታተላል፤ ለህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ደረጃ ያወጣል፣ ያድሳል፡፡

12) Oofaanotenna gogo'maasinete ikkadimmate buuxishsha uytanno; haaroonsitanno; ittissanno; hooltanno.
13) Oofaanchu ikkadimma uuxishshi keenonna tekinikete ogeeyye qajeelshi mereershuwa uurrissanno; qajeelsha uytanno; yannate tekinoloojenni irkisantanno gede assitanno.
14) Dagatenna hogowu gongo'maasine kunseenna uurritaano gede assitanno; aye bisinnino loosamannoha daddalu gongo'maasinchi kunseeni deerri bikkaasincho fushshitanno; gashshitanno; ha'runsitanno; kunseenu giddo qorqorsha assitanno; jeefishubiddissa fushshitanno.
15) Doogote hodhishshi seeri ayirrisamasi ha'runsitanno; qaafo adhitanno.
16) Motorete gongo'maasine aana qa'minsanni saleeddanna hodhishshu borro attansiissanno; tuqissanno.
17) Qoqqowu doogote adawi womaashshu buenna amaalaancho kawunsile uurrissanno.
18) Kalaqamunnitinna mannu loosino dano kalaqantanno woyte woy wole hasiisaano korkaatubbanni daddalu gongo'maasine hasiisanno darganna raga qolte qeechite bobbaassanno; ha'runsitanno.
19) Wole qeechigutamaano bisubba ledo doogote tiraafikete dano gargarate waacante loossanno.
20) Hexxo jeefo gansiissannota wole assootubbano loossanno.

12) ለአሽከርካሪዎችና ለተሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፡፡
13) የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና እናየቴክኒሻኖች ማሰልጠኛ ማዕከላት ያቋቁማል፣ ስልጠና ይሰጣል፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ያደርጋል፡፡
14) የሕዝብና የጭነት ማመላለሻ መናኸሪያዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣ በማንኛውም አካል የሚሰራ የንግድ ተሽከርካሪ መናኸሪያ ደረጃ መለኪያ ያወጣል፣ ያስተዳድራል፣ ይከታተላል፣ በመናኸሪያ ውስጥ ቁጥጥር ያደርጋል፣ ለአፈፃፀሙ መመሪያ ያወጣል፡፡
15) የመንገድ ትራንስፖርት ሕጎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ እርምጃ ይወስዳል፡፡
16) ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ላይ የሚለጠፉ ሰሌዳዎችንና የትራንስፖርት ህትመቶችን ያሳትማል፣ ያሰራጫል፡፡
17) በክልሉ የመንገድ ደህንነት ፈንድና ካውንስል ያቋቁማል፡፡
18) የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ሲከሰት ወይም በሌሎች አስፈላጊ ምክንያቶች የንግድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በአስፈላጊው ቦታና መስመር ደልድሎ ያሰማራል፣ ይከታተላል፡፡
19) ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የመንገድ ትራፊክ አደጋ ለመከላከል በቅንጅት ይሠራል፡፡
20) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 20. Industirete Latishshi Biiro

1) Qoqqowu giddo Industire hala'litanno gede hasiisanno amuraate diriisite injaannori kalaqamanno assitanno.
2) Industiretenna ogimmate lifinxe keenate seera loosu aana hosiissanno, silaanchimanna udiinnichu deera hajo la'anonsa bisubba ledo halamatenni tajete woraqatinni buuxantanno gede irko assanno, laashshu isilaanchimma deera afidhanno gede loossanno;
3) Industirete irko paakeeje qixxeessitanno, qineessitanno, jeefisiissanno, loosu aana hosaseno ha'runsitanno.
4) Industirete qachubba, sheedubba, paarkubbanna kilaasterubba halashshitanno, gatamartanno, hasiisanno qorqorshsha assitanno.
5) Indestrubbate dikkote Mereersha urrissanno, Qineessitanno, injeessitanno,
6) Indesitirete handaara baxxinohunni maanufakicheringete indesitire latishshunna heewisaanchimmate aana loossanno, tenneno buuxisissanno poolise istiraateeje, pirogiraamenna seerra burqissanno, Goboomu lophote latishu ragi timo ledo sumuu yaase buuxxanno, konneno buuxisiisate titirshunni meriha gibire qixeessanno, hajo la'anno bisinni kaajjanno woyteno loosu widira eessanno.
7) Maanufakicheringete Indesitirete hanadaari hallanyu beeqqqonna qeecha lossatenna jawaachishate

## 20. የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

1) በክልሉ ኢንደስትሪዎች እንዲስፋፉ ተገቢ ሥርዓት በመዘርጋት የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡
2) የኢንዱስትሪ የሙያ ብቃት መመዘኛ ሕጎችን በስራ ላይ ያውላል፣ የጥራት እና የምርቶች ስታንዳርድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በምስክር ወረቀት እንዲረጋገጥ ድጋፍ ያደርጋል፣ የምርት ጥራት ደረጃ እንዲያገኙ ይሰራል፡፡
3) ኢንዱስትሪዎች የድጋፍ ፓኬጅ ያዘጋጃል፣ ያቀናጃል፣ ያስፈጽማል፣ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡
4) ኢንዱስትሪ መንደሮች፣ ሼዶች፣ ፓርኮች እና ክላስተሮች እንዲስፋፉ፣ እንዲጠናከሩ ያደርጋል፣ አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
5) የኢንደስትሪ የግብይት ማዕከላትን ያቋቁማል፤ ያስተባብራል፡ ያመቻቻል
6) የኢንደስትሪ ዘርፉን በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንደስትሪ ልማትና ተወዳዳሪነት ላይ ይሰራል፤ ይህንንም የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን ስትራቴጂዎችን ፕሮግራሞችንና ህጎችን ያመነጫል፤ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ግብ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፡ ይህንንም ለማረጋገጥ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፡ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ወደ ስራ ያስገባል፡፡
7) በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግና ለማበረታታት

kaa'litanno loosu amuraate diriirsitanno, injo qineesitanno, titirshu wodhotenni fulanno.

8) Maanufakicheringete handaari illachisha hasiissannonsa hoccunna hoccuullu, gogu; sagaletenna agattote indasitirranna wolootu hasiishinsa luphi yiino cinaano indesitirete handaarra baddanno, goboomu latishu ragi timo ledo sumu yaase buuxxanno, tenneno jeefisiisate titirshu looso qixeessite hajo la'asi bisi kajishiro loosu aana hosiissanno.

9) Indesitirete handaarira egenno halashate xinxallo assitanno bissa hasiissanno irko assatenni indesitirennita invesitimentetenna manufakicherte dhuki heewisaanchimma luphi yitanno gede dancha rosicho hadhe xaphoomu zarifete gumamimma sooronna lopho abbitara loossanno.

10) Manufakicherennita hattono wolootu invesiterete handaari gumi Silaanchimmanna agarinohanna kalqete deerinni heewisamaancho ikkanno gede dhuka dhabbachishate looso loossanno.

11) Hajo la'ansa bissa ledo halamatenni Indestirete handaara baxxino garinni manufakichere hasiisannoha mannu hasattonna uduunne wonshate hayyo kalaqqanno, qineessitanno, loosu aana hosiissanno;

12) Indestirete handaara baxxino garinni manufakichere latishunna gumaamimma lossate ekisteenshinete

የሚያስችል የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፤ ምቹ ሁኔታ ያመቻቻል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወጣል፡፡

8) በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን የጨርቃ ጨርቅ፤ የቆዳ፡ የምግብና የመጠጥ ኢንደስትሪዎችን እና ሌሎችም የመሳሰሉት ንዑስ ዘርፎች ካላቸው ጠቀሜታና እምቅ አቅም አንፃር ይለያል፤ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ግብ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፡ ይህንንም ለማረጋገጥ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፡ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ወደ ስራ ያስገባል፡፡

9) በኢንደስትሪው ዘርፍ ምርምርና ጥናት ለሚያካሂዱ አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የኢንደስትሪዎችን የኢንቨስትመንትና የማኑፋክቸሪነግ አቅምና ተወዳደሪነት እንዲያድግ ያደርጋል፡ ምርጥ ተሞክሮ ይቀምራል፤ አጠቃላይ በዘርፍ አዎንታዊ ለውጥና እድገት እንዲመጣ ይሰራል፡፡

10) የማኑፋክቸሪንግ እንዲሁም ሌሎች የኢንደስትሪ ዘርፎች የምርት ጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲኖራቸውና በአለም ዐቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ማጎልበት፤የስርፀት ስራዎችን ይሰራል፤

11) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢንደስትሪ ዘርፉን በተለይም የማኑፋክቸሪነግ ዘርፉ አስፈላጊ በሆነ የሰው ሀይል ፍላጎትና አስተማማኝ ግብዓት ለማሟላት ስልት ይቀይሳ፤ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

12) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትና ምርታማነትን

owaante, tekinolooge, dikkonna guma batisate ha’rinshora irko assitanno, gumaamimmansa buuxxanno.

13) Shiimaadda, mereerima, jawiidi manufakicherete indestirubba mereero qinaabbino xaadooshshi kalaqaramanna gumaamo loosa, poolise , istiraateejenna loosu amuraate diriirsitanno;

14) Shiimmaddanna mereerima interprayizooti gumaamma ikkitanno gede hayyo kalaqqanno, irko assitanno.

15) Indestirete handaara baxxino garinni manufakicherete qarqaru agarooshira worronni safaraancho wonshitara irko assitanno.

16) Indestirete handaarunna ogimmate Maamarra uuritanno gede jawachishanno, uritinorino jawattanno gede assitanno.

17) Hexxo jeefo gansiisate kaa’lannoha wole assootubba assitanno

**21. <u>Quchumunna Xinti Latishshi Biiro</u>**

1) Quchumu latishshanna konistiraakshiine la’anno polisenna istiraateeje, latishshu paakeejenna pirogiraamma suudissanno; kaajjitanno woyteno loosu aana hosiissanno;

2) Quchumu teesaano ikkitino daga dhukinsa ledo darawoo’mino mine mi’nitara xaphooma raga leelisha dandiissitanno xiinxallo ha’rissanno; loosu



ለማሳደግ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓትና የግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፤

13) በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠርና ስኬታማ ሽግግሮች እንዲከናወኑ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤

14) የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ውጤታማ እንዲሆኑ የማትጊያ ስልት ይቀይሳል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

15) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ያደርጋል፤

16) የኢንዱስትሪ፣ የዘርፉ እና የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲበረታቱ ያደርጋል።

17) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

**21. <u>የከተማና መሠረት ልማት ቢሮ</u>**

1) የከተማ ልማትንና ኮንስትራክሽንን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን፣ የልማት ፓኬጆችን እና ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ሲጸድቅም፣ ተግባራዊ ያደርጋል።

2) የከተማ ነዋሪ የሆነ ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ መኖሪያ ቤት እንዲሰራ አጠቃላይ አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችሉ ጥናቶችን

aana hosansa garano quchumuwate dhuka kaajjishate irko assitanno.

3) Quchumuwannita deerru keenonna deerra murtanno; afansha afidhanno gede assitanno.
4) Quchumuwa qarqarinsara latishshu mereersha ikkitara qinaabbino irko assitanno.
5) Quchumuwate latishshi baadiyyete latishshinna buximate ajishshi ledo qinaawino garinni loosamanno gara lainohunni xiinxallo assitanno; xiinxallo loosu aana hossara irko assitanno; gumulaanchimma ha’runsitanno.
6) Quchumuwate yannillaanchu safote latishshi hala’lanno gede jawaantetenni loossanno; isimart siti goboomu raga hedote giddo woratenni quchumma heeshshote injiitanno gede assate loossanno.
7) Qoqqowu quchumuwa pilaane qixxeessitanno; loosoho hosansa gara ha’runsitanno; irko assitanno.
8) Quchumu pilaane qixxaawora bobbakkanno amaalaanora ikkadimmate buuxishsha uytanno; deerransa murtanno; fajjoote uytanno; hooltanno.
9) Quchumuwatenni fultannore moola ishine hunatenna biifado gangalatto owaante safantannoha assootu amuraate diriirsitanno; irko assitanno.
10) Quchumuwate latishshinna danchu gashshooti loosi aana teesaano qinaawaancho doogonni beeqqitanno gede dandiissate assooti amuraate diriirsitanno; gumulsiisaanchimmat e dhuka kaajjishshanno; buusansiissanno; guunte ha’runsitanno.

ያካሂዳል፣ ለተግባራዊነታቸውም ለከተሞች የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል።

3) የከተሞችን የደረጃ መመዘኛና ደረጃ ይወስናል፣ ዕውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል።
4) ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል።
5) የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት እና ከድህነት ቅነሳ ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናት ያደርጋል፣ ጥናቱ ተግባራዊ እንዲሆን ያግዛል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል።
6) በከተሞች ዘመናዊ መሰረተ-ልማት እንዲስፋፋ ጥረት ያደርጋል፣ የስማርት ሲቲ ሀገራዊ አቅጣጫዎችን ከግምት በማስገባት ከተሞች ለኑሮ እንዲመቹ ይሰራል።
7) የክልሉን ከተሞች ፕላን መዘጋጀቱንና መተግበሩን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል።
8) በከተማ ፕላን ዝግጅት ለሚሰማሩ አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል ደረጃቸውን ይወስናል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይሰርዛል።
9) ከተሞች የሚያመነጯቸውን ደረቅ ቆሻሻዎች የሚወገድበትንና ውበት ያላቸው የመናፈሻ አገልግሎቶች የሚመሰረቱበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ድጋፍ ያደርጋል።
10) በከተሞች የልማትና መልካም አስተዳደር ሥራዎች ላይ ነዋሪው ህዝብ በተደራጀ አግባብ እንዲሳተፍ ለማስቻል የአሠራር ስርዓት ይዘረጋል፣ የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤

11) Minate latishshi pirogiraamma massagganno; tekinikaancho irko assitanno; illaallissanno; quchumu manni hee'ranota taalcho minna mi'nara hayyo maltanno; loosu aana hosa ha'runsitanno.
12) Loosu aana noo wolootu seerubanni quchumunna xintu latishshi biirora uynoonni biilloonyinna loosu qeechi konni lallawinni uurritino quchumunna xintu latishshi biirora uynoonni;
13) Hexxo jeefo gansiisate kaa'liatannota wole assootubba assitanno.

**22. <u>Way, Shiilotenna Inerjete Biiro</u>**

1) Qoqqowunnita way jiro gashshitanno.
2) Qoqqowunnita qiletenna aaniidi way jiro bikkunninna silanchimmatenni baddanno; horote hosanna gara injeessitanno.
3) Way latishshinna gashshooti maanuwallanna deerra qixxeessitanno; woleno way loosi gola illaallissanno.
4) Anganni way shiqisho tittirshi xiinxallo assitanno; gimbaata assitanno.
5) Quchumunna baadiyyennihu xalalu way shiqisho tuqo lophanno gede assitanno; deerra murtanno; tekinikaanchu loosi guunte ha'runsitanno.
6) Baadiyyete way uurrinshuwa gashshooti komitta uurrissanno; seeraancho mannimma fajjoote uytanno;

ያስተባብራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

11) የቤቶች ልማት ፕሮግራሞችን ይመራል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ የመኖሪያ ቤት እንዲሰራ ስልት ይቀይሳል፣ተግባራዊ ነቱን ይከታተላል፡፡
12) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለከተማና መሠረት ልማት ቢሮ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ለከተማና መሠረት ልማት ቢሮ ተሰጥተዋል፤
13) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**22. <u>የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ</u>**

1) የክልሉን የውሃ ሀብት ያስተዳድራል፡፡
2) የክልሉን የከርሰ ምድርና ገፀ ምድር ውሃ ሀብት በመጠንና በጥራት ይለያል፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
3) የውሃ ልማትና አስተዳደር ማኑዋሎችንና ደረጃዎችን ያዘጋጃል እንዲሁም ሌሎች የውሃ ሴክተር ስራዎችን ይቆጣጠራል፡፡
4) የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ዝርዝር ጥናት ያጠናል፣ ግንባታዎችን ያከናውናል፡፡
5) የከተማና ገጠር የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን እንዲያድግ ያደርጋል፣ ደረጃውን ይወስናል፣ የቴክኒካዊ ሥራዎችን አፈፃፀም ይከታተላል፡፡
6) የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት አስተዳደር ኮሚቴዎችን ያደራጃል ሕጋዊ የሰውነት ፈቃድ

quchumu way owaante uurrinshuwa xintitanno.

7) Qoqqowoho way du’namme farcamaanchimmanna taalashshu way beehaachi qeechi hee’rasi illaallissanno.
8) Way anje noo qoqqowu qarqarubbara winaamu yanna way shiqisho injeessitanno; qarrano hegerimmatenni hunate dandiissanno looso loossanno.
9) Way bisubba burquuqamme gargartanno; qorqortanno; cingaanno ishine hoollanni hayyo diriirsitanno; way akeeka gamba assitanno; laaboraatoorete fonqolsha assitanno.
10) Wayinna gorsu latishshi loosira bobbakkanno tequwaraacera, amaalaanoranna ogeeyyera deerra murtanno; loosu fajjoote uytanno; haaroonsitanno; ittissanno; hooltanno.
11) Qoqqowunniha gorsu latishshi tuqo lossate gorsu latishshinna meemiishshu loosi xiinxallonna diizayne looso loossanno; gimbaatu carata qixxeessitanno; loosoho hosiissanno.
12) Laggate du’nama ragi biddonna lolahu gargarooshshi loosi xiinxallo diizaynenna gimbaatu qorqorshi looso loossanno.
13) Qoqqowoho assinanni gorsu konistiraakishiine loosi safaraano qixxeessitanno; loosoho hasiisa massagganno.
14) Gorsu aggaxxo xiinxallo, diizaynenna gimbaati looso massagganno; ha’runsitanno; illaallissanno; dhuka

ይሰጣል፣ የከተማ ውሃ አገልግሎት ድርጅቶችን ያደራጃል፡፡

7) በክልሉ የውሃ ተፋሰሶች ፍትሐዊና ሚዛናዊ የውሃ ክፍፍልና ምደባ መኖሩን ይቆጣጠራል፡፡

8) የውሃ ዕጥረት ባለባቸው የክልሉ አካባቢዎች የአስቸኳይ ጊዜ የውሃ አቅርቦት ያመቻቻል፣ ችግሩንም በዘለቄታዊነት ለማስወገድ የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

9) የውሃ አካላት ብክለትን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ ፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ስልት ይቀይሳል፤ የውሃ ናሙና ይሰበስባል፣ የላብራቶሪ ምርመራ ያደርጋል፡፡

10) በውሃና በመስኖ ልማት ስራ ለሚሰማሩ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሞያዎች ደረጃቸውን ይወስናል፣ የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፡፡

11) የክልሉን የመስኖ ልማት ሽፋን ለማሳደግ የመስኖ ልማትና የማጠንፈፍ ሥራዎች ጥናትና ዲዛይን ያከናውናል፣ የግንባታ ጨረታ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

12) የወንዞች ፍሰት አቅጣጫ መግራት እና የጐርፍ መከላከያ ሥራዎች ጥናት ዲዛይንና ግንባታቁጥጥር ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

13) በክልሉ የሚካሄዱ የመስኖ ኮንስትራክሽን ሥራዎች መስፈርት ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱን ይመራል፡፡

14) የመስኖ አለኝታ ጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

kaajjishshanno.

15) Qoqqowu mootimma widoonni minnoonnita gorsu uurrinshuwa qorobbanno; gatamartanno; gorsu uurrinshuwa qarqaru ogeeyye qajeelshatenni qorobbannonna gashshitanno gede iillishshanno.

16) Federaalete mootimma widoonni qoqqowu giddohadhanno way latishshi pirojektuwa assootira annimmatenni irko assitanno.

17) Qoqqowu gede loosamanno Shiilo hasatenna latisate loossa aliidimmatenni massaganno; harunsitanno.

18) Qoqqowu gede Inerjete buichonna doorsha halashshate, latisatenna horonsirate amuraate sirsitanno; jeefishshasino harunsitanno.

19) Hexxose jeefisate kaa'liatannota wole loossa loossanno.

### 23. <u>Meyate, Wedellunna Dagoomite Hajubba Biiro</u>

1) Meyate, qaaqquullunna wedellu qoossonna horo ayirisiisate qooxeessa hegerrenna millimmo kalqantanno gede assitanno.
2) Heewisamaanonna baqqiima qansichoota kalaqate kaa'liatannota fayyo maate kaajjishshi pirogiraamma halamaano bisubba ledo qinaawatenni suudissanno; loosoho hosanna gumaa'mate gara ha'runsitanno; illaallissanno.
3) Meentu, qaaqquullunna wedellu ikkito mu'lissannota tittirancho mashalaqqe gamba assitanno; qineessitanno; la'annonsarira baalanko egennantanno gede asitanno.
4) Meentunna wedellu qoqqowoho polotiku, miinjunna

አቅም ይገነባል።

15) በክልሉ መንግስት አማካኝነት የተገነቡ የመስኖ ተቋማትን ይንከባከባል፣ ይጠግናል፣ የመስኖ ተቋሞችን በአካባቢው ሙያተኞችን በማሰልጠን እንዲንከባከቡና እንዲያስተዳድሩ ያበቃል።

16) በፌደራሉ መንግስት አማካኝነት በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የውሃ ልማት ፕሮጀክቶች ክንውን በባለቤትነት ድጋፍ ያደርጋል።

17) በክልሉ የሚካሄደውን የማዕድን ፍለጋና ልማት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል።

18) በክልሉ የኢነርጂ አማራጮችን የማስፋት፣ የማልማት እና የአጠቃቀም ሥርዓትን ይዘረጋል፣ አተገባበሩንም ይከታተላል።

19) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

### 23. <u>የሴቶች፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ</u>

1) የሴቶች፣ የሕፃናትና የወጣቶች መብትና ጥቅሞችን በማስከበር ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል።
2) ተወዳዳሪና ንቁ ዜጋን ለማፍራት የሚረዱ የጤናማ ቤተሰብ ግንባታ ፕሮግራሞችን ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት ይቀርጻል፣ ተግባራዊነቱንና ውጤታማነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
3) የሴቶችን፣ የሕፃናትና የወጣቶችን ሁኔታ የሚያመላክቱ ዝርዝር መረጃዎችን ይሰበስባል ያደራጃል፣ በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል።
4) ሴቶችና ወጣቶች በክልሉ የፖለቲካ፣

dagoomu mittoomu millimmuwa giddo baqqiima ikkite beeqqate dandiissiissanno kaayyo injiitinonsata buuxxanno.

5) Meyatinna wedellu hasattonsanna mitiimmansa garinni qinaabbe qoossonsara sharrantaranna mitiimmuwansa huna dandiitara jawaachishshanno; ikkito injeessitanno.

6) Qoqqowu mootimma bisubbanni qixxaabbanno polisubba, seerubba, latishshu pirogiraammanna pirojektuwa meyatenna wedellu hajo hanqaffanno gede hayyo maltanno; keentanno; gara ikkitino ha’runso assitanno.

7) Qeedhootanna wedella mereersite babbaxxitino uurrinshuwara loosantanno loossa ha’runsitanno; buusansiissanno keentanno; taashshaancho qaafo adhitanno; tittirshu biddissunni muramanno.

8) Meentunna qaaqquullu aana iillanno gosoonshanna qohaano rosichu ikkituwanna qonke xiinxallotenni badatenni ba’anno gara injeessitanno; gumulaanchimma ha’runsitanno; hegerre cu’mishiishate looso loossanno.

9) Meentu babbaxxitino mootimmate bisubbara muro aate loosi darguwara qeechamate ikkado illacha tungoonninsata buuxxanno.

10) Woriidi heeshshote deerrira afantanno meenti heeshsho gara woyyeessate kaa’litanno xiinxallo ha’rissanno; pirogiraammanna pirojektuwa qixxeessatenni loosoho hossanno assitanno; liqootenna suuqote owaante afidhanno gara

የኢኮኖሚና ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችላቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል።

5) ሴቶችና ወጣቶች እንደ የፍላጎቶቻቸውና እንደ ችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

6) በክልሉ መንግስት አካላት የሚያዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል።

7) ወጣቱን ማዕከል አድርገው በተለያዩ ድርጅቶች የሚሰሩ ስራዎች ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይገመግማል፣ ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

8) በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚቃጡ መድሎዎችን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶችን በጥናት በመለየት የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፣ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራል።

9) ሴቶች በተለያዩ የመንግስት አካላት በውሳኔ ሰጪ የስራ ቦታዎች ላይ ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል።

10) በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ አፈጻፀሙን

injeessitanno; gumulaanchimma ha'runsitanno.

11) Meentunna wedellu latishshu, danchu gashshootinna dimokiraasete amuraati kaajjishshira baqqiima beeqqaanonna horaameeyye ikkitara hayyo maltanno; irko assitanno.

12) Meentunna wedellu xintamooshshi dhuka owirsate dandiissiissanno xiinxallo ha'rissanno; qajeelshuwa uytanno; qajeelshu owaante aamantanno assoote injeessanno; buusansiissanno.

13) Amuwu heeshsho woyyaabbannonna qaaqquullu qoossonna adawi agaramanno gara xiinxallitanno; la'annonsa bisubba ledo buusamatenni loosoho hosiisanno.

14) Qoqqowoho meentunna qaaqquulle la'annota gobbanke kalqoomu deerrinni malaatisse adhitino sumiimmuwa gumulaanchimma ha'runsitanno; la'annonsa bisubbara rippoorte shiqishshanno.

15) Bisu muso noonsari, geeru, surrete xisso noonsarinna labbanno addi illacha hasidhanno dagoomu bissa kaa'lonna irko afidhanno mereershubba xintantanno gede hajo la''anonsa bissa ledo waaxotenni loossanno.

16) Hexxo jeefa gansiisate kaa'liatannota wole assootubba assitanno.

**24. <u>Wogate, Turizimetenna Ispoortete Biiro</u>**

1) Qoqqowoho afantannori dhaggete, budu donnanna hornyuwa xiinxallantara, agarantara sayinsenna tekinoloojete owaantera hossanno gede assitanno.

ይከታተላል፡፡

11) ሴቶችና ወጣቶች በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ላይ ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስልት ይቀይሳል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

12) የሴቶችና የወጣቶች አደረጃጀቶችን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ የስልጠና አገልግሎትየሚሰጥበትን አሰራር ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፡፡

13) የእናቶች የኑሮ ሁኔታ ስለሚሻሻልበትና የሕፃናት መብትና ደህንነት ስለሚጠበቅበት ሁኔታ ያጠናል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

14) በክልሉ ሴቶችንና ሕጻናትን የሚመለከቱ ሀገራችን የፈረመቻቸው አለምአቀፍ ስምምነቶች አፈጻፀም ይከታተላል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፡፡

15) የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የአእምሮ ሕሙማንና መሰል ልዩ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙባቸው ማዕከላት እንዲደራጁ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

16) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**24. <u>የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ</u>**

1) በክልሉ የሚገኙ ታሪካዊ፣ ባህላዊ ቅርሶችና እሴቶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁ ለሣይንስና

2) Sidaamu Afii borreessamme bowirtaranna hala'litara hayyo malatenni loossanno.
3) Deerrasi agarrohu loosu afii horoonshinna tiro heedhanno gede irko assitanno; ha'runsitanno.
4) Qohaano rosichu assootubba hekko korinni dagoomu lopho badhera qoltanno lao, ammanonna rosichu assootubba soorrate looso loossanno.
5) Qoqqowu latishshira kaa'lo afidhinore budu amanyootuwanna rosicho hala'lao gede assitanno.
6) Budu handaarira dagate beeqqo uurrinshaawe safo amadisiisate budu uurrinshuwa hala'litao gede assitao.
7) Angichu ogimmanna seesi-qalote loosi hala'lanno gede assitanno; latishshaho noonsa kaa'lo garinni kaajjishate handaaru taje yannitte doogonni xintantanno gede assitanno; tuqisamansano buuxxanno.
8) Qoqqowu giddo aye manchi, maamaru, amm'note uurrinshanna wole uurrinsha anga afantanno donna seekkite amadantannonna agarantanno gede irko assitanno; borreekkissitanno (borreesse maareekka); qorqortanno; daa''attote (reqeccote) amadantino donna, dubbu saadanna gumansa haadhe gara doogonni gashshitanno.

ቴክኖሎጂ አገልግሎት እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

2) የሲዳሙ አፎ ሥነጽሑፎች እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ስልቶችን በመቀየስ ይሰራል፡፡

3) ደረጃውን የጠበቀ የሥራ ቋንቋ አጠቃቀም እና የትርጉም አገልግሎት እንዲኖር ይደግፋል፣ ክትትል ያደርጋል፡፡

4) በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተፅእኖ ሳቢያ ማኅበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፤ እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

5) ለክልሉ ልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ባህላዊ ሥርዓቶችና ልምዶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡

6) በባህል ዘርፍ የሕዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡

7) የዕደ ጥበብ፣ የኪነ ጥበብና የሥነጥበብ ሥራዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ ለልማቱ የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ ለማጎልበት የዘርፉን መረጃዎች በዘመናዊ መንገድ እንዲደራጁ ያደርጋል፣ ተደራሽነቱንም ያረጋግጣል፡፡

8) በክልሉ ውስጥ በማንኛውም ሰው፣ ማህበር፣ የሐይማኖት ድርጅት ወይም ተቋም እጅ የሚገኙ ቅርሶች በሚገባ እንዲያዙና እንዲጠበቁ ድጋፍ ይሰጣል፣ ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል፣ በኢግዚቪትነት የተያዙ ቅርሶችን፣ የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸውን ተቀብሎአግባብነት ባለው መንገድ ያስተዳድራል፡፡

9) በዘርፉ ውጤታማ የፈጠራ ሥራዎችን ሳበረከቱ

9) Handaaraho gumaamo qaltote looso ba’raassino hojjimmootiranna uurrinshuwara ba’raarshunna jawaachishshu aamamanno amuraate diriirsitanno; loosohono hosiissanno.

10) Qoqqowoho filmete tewuneete ogimma loosi lophanno gara injeessitanno.

11) Qoqqowuita turizimete lii’lachuwanna dancha illacha egesiissao; turizime qoqqowoho hala’litao gede jawaachishshao.

12) Qoqqowuita turistete lii’lachuwa axxite egentannonna turizimete injaado ikkite latisataranna qinaabbara, turistete owaante uytanno uurrinshuwa hala’liara, qarqaru qarqarunkunni noo dagoomino turizimete horonni eeqqaancho ikkara assinanni eero injeessitanno.

13) Qoqqowunniti kalaqamu donna xiinxallantanno gede. Agarantanno gedenna, turizimete injaado ikkite lattannonna horote hossanno gede assinanni gara injeessitanno; gooomu deerrinni balaxooshshimmatenni ofoltino safaraano wonshatenni qoqqowu donna kalqete donimmara orreekkantanno gara la’annonsa bisubba ledo injeessitanno.

14) Budunna turistete owaante uytanno uurrinshuwa deerra murtanno; gumulanchimma illaallissanno.

15) Turizimetenni guuta owaante heedhara turistootu hoaatino buuxamara hasiisannohu duuchu manniti loosu waacamme adda ikkitara kalaqantannota gutu



ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፡፡

10) በክልሉ የፊልም ተውኔት ጥበብ ሥራዎች የሚያድጉበትን አግባብ ያመቻችል፡፡

11) የክልሉን የቱሪዝም መስሕቦችና መልካም ገፅታ ያስተዋውቃል፤ ቱሪዝም በክልሉ እንዲስፋፉ ያበረታታል፡፡

12) የክልሉን ቱሪስት መስሕቦች ተለይተው እንዲታውቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ፣ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉ፣ የየአካባቢው ማኅበረሰብም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካፋይ እንዲሆን የሚደረግበትን አግባብ ያመቻቻል፡፡

13) የክልሉ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጡ መስፈርቶችን በማሟላት የክልሉ ቅርሶች በአለም አቀፍ ቅርስነት የሚመዘገቡበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያመቻቻል፡፡

14) የባህልና የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፡፡

15) በቱሪዝም የሠመረ አገልግሎት እንዲኖር የቱሪስቶችም ደህንንት እንዲረጋገጥ የሚያስፈልገው የብዙ ወገኖች የሥራ ቅንጅት

battala mereershunni owaattanno.

16) Turistete doogonna la’nanni darguwa loosantaranna qinaabbanno gede assitanno; la’anno bisubba ledo buusamatenni qoqqowu giddo ha’rinsanni safote latishshi gimbaatanna wole qarqaru latishshi millimmo turizime irkissano garinni ha’ransa ha’runso assitannno.

17) Seerunni murrannni owaante dani qarichimoota safo assidhe qoqqowu giddo loossanno turistete owaante uytanno uurrinshuwara deerra uytanno; hakko deerra agadhite ikkadimmanna silanchimma noo owaante aansa ha’runsitanno; illaallissanno; gadachonsa fultannokkiri aana taashshate qaafo adhitanno; adhisiissanno.

18) Mannu wolqa qajeelshinnninna ogimmate amaale widoonni budu, ispoortetenna turizimete goliha gumulsiisate dhuka kaajjishshanno.

19) Sidaamu daga heeshsho gara, saga’late gara, uddi’rate gara, gashshatenna wole hornyuwa gara gobboomunna kalqoomu deerrinni egennantanno gede loossanno.

20) Qoqqowoho babbaxxitino gangalattonna doorshunni mannu loosino turizime mereerishi gimbaata loossanno; gashshitanno; halashshitanno.

21) Budu, ispoortetenna turizimete taje gamba assitanno; qineessitanno; tuqissanno.

22) Daga ispoorte baalunkuranna budu ispoorte

እውን እንዲሆን ለሚፈጠሩ የጋራ መድረኮች በማዕከልነት ያገለግላል፡፡

16) የቱሪስት ጉዞ መስመሮችና መመልከቻ ቦታዎች እንዲሠሩና እንዲደራጁ ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችና ሌሎች የአካባቢ ልማት እንቅስቃሴዎች ቱሪዝምን በሚደግፍ መንገድ ስለመካሄዳቸው ክትትል ያደርጋል፡፡

17) በሕግ የሚወሰነውን የአገልግሎት ዓይነት ስታንዳርድ መሠረት አድርጐ በክልሉ ውስጥ ለሚሰሩ የቱሪስት አገልግሎት ሠጭ ድርጅቶች ደረጃ ይሰጣል፣ ይህንኑ ደረጃ ጠብቀው ብቃትና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ግዴታቸውን በማይወጡት ላይም የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ያስወስዳል፡፡

18) በሰው ኃይል ሥልጠናና በሙያ ምክር አገልግሎት አማካይነት የባህል፣ የስፖርትና የቱሪዝም ሴክተርን የማስፈጸም አቅም ይገነባል፡፡

19) የሲዳማ ሕዝብ የአኗኗር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ የአስተዳደር እና ሌሎች እሴቶችበሀገርና ዓለም አቀፍ ደረጃ በተገቢው እንዲታወቁ ይሰራል፣

20) በክልሉ የተለያዩ የመዝናኛና አማራጭ ሰው ሰራሽ የቱሪዝም ማዕከላትን ይገነባል፣ ያስተዳድራል፣ ያስፋፋል፡፡

21) የባህል፣ ስፖርትና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፡፡

beeqqaanonna horaameeyye assitanno.

23) Qajeelino manni wolqa burqisanna ikkadimma lossate ispoortete rosi, qajeelshinna xiinxallote uurrinshuwa uurritanno hayyo malatenni loosoho hossanno gede assitanno.

24) Ispoortete wo’naalshi darguwanna ispoortete bowirshi mereershuwa halashshitanno.

25) La’annonsa bisubba ledo buusamatenni ispoortete xagishshi owaante uurrissanno.

26) Ispoortete garimalu jawaachishshi dhagganna araadote udiinne horoonsi’ra gargarate dandiissanno amuraate diriirsitanno.

27) Heewonna feestivaale qixxeessatenni ispoortete handaarita eote safo halashshitanno; dagoomu beeqqonna horaameessimma lossitanno.

28) Qoqqowoho uuritanno ispoortete mamarrara fajoote uytanno; qorqortanno; irkissanno; buusansiissanno; investerootu ispoortete handaara e’e beeqqo assitanno gara injeessitanno; federaalete deerrinni uurritino ispoortete maamarra borreekkitanno; hasiissanno irko assitanno.

29) Hexxo jeefa gansiisate kaa’liatannota wole assootubba assitanno.

**25. <u>Loosunna Dandoote Biiro</u>**

1) yuniversitete, kolleejuwatenni, pooli teekinikete kolleejuwanninna babbaxino deerrini rosse guddino hattono taxi assite looso tirtinore ikkatenni uurritino

22) ህዝቡን በስፖርት ለሁሉምና ባህላዊ ስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡

23) የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራትና ብቃትን ለማሳደግ የስፖርት ትምህርት፣ ሥልጠናና ምርምር ተቋሞች የሚቋቋሙበትን ሥልት በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

24) የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችንና የስፖርት ማበልጸጊያ ማዕከላትን ያስፋፋል፡፡

25) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ህክምና አገልግሎት ያደራጃል፡፡

26) በስፖርት አበረታች መድሃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

27) ውድድሮችንና ፌስቲቫሎችን በማዘጋጀት የስፖርቱ ዘርፍ የገቢ መሠረቶችን ያሰፋል፣ የህብረተሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ያሳድጋል፡፡

28) በክልሉ ለሚቋቋሙት የስፖርት ማህበራት ፍቃድ ይሰጣል፣ይቆጣጠራል ፣ይደግፋል፣ያስተባብራ ል፣ ኢንቨስተሮች በስፖርት ዘርፍ ገብተው ኢንቨስት እንዲያደርጉሁኔታውን ያመቻቻል፣ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

29) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**25. <u>የሥራና ክህሎት ቢሮ</u>**

1) ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከኮሌጆች፣ ከፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችና በተለያዩ ደረጃዎች ተምረው ያጠናቀቁ

maayikironna shiimamadda interpiraayize faynaanse shiqishanonna Liizete uduunne shiqishanno uurrinshuwa ledo ikkatenni liqoote, maashinetenna wo’ma indusitire ekisteenshinete Owaante afi’dhanno gara injeessitanno;

2) mittu bayichi Owaante uynanni mereershubba tantananno, jawaachishanno, bilchaatino Owaante aate dandisiisanno woyyaawino haro amuraate diriirsitanno, mereershubbate wolqa dhabachiishshanno;

3) Qoqqowu giddo looso hasidhanno addinnii wedellunna meyati looso kalaqate hala’ladunni bobbakkanno gede huwanyo kalaqate, qajeelishunni irkisate, loosu base injeesate, liqoote, dikkote xaadooshshi amaalenna woloota kaa’lo afidhanno gede assitanno; injo kalaqqanno.

4) Interpirayzete irko paakeeje qixxeessitanno, qineessitanno, jeefisiissanno, loosu aana hosaseno ha’runsitanno.

5) Manufakcherete laalcho baara widira sokkanno Interpirayzoota hajo la’annonsa bisubba ledo halamatenni laalchonsa baara widira sokkanno gede irkissanno.

6) Loosu kaayyo kalaqate amaale mini baalante tantanora uurranno gede assitanno, amaalete minira looso qineesitanno, hasiissanno irko uyitnno.

7) Looso kalaqatenna loosu kaayyo aana xiinxallo assitanno, hajo la’annonsa bisubba shiqishatenni kaajjishiishidhanno, gumulo loosu aana hosase ha’runsitanno.

እንዲሁም አቋርጠው ስራ አጥ በመሆን ለተቋቋሙ የማክሮና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ከፋይናንስ አቅራቢና ከሊዝ መሳሪያ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር በመሆን የብድር፣ የማሽንና የሙሉ ኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

2) አንድ ቦታ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ያደራጃል፣ ያጠናክራል፤ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የተሻሻሉ አዲስ ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣ የማዕከላቱን አቅም ይገነባል፤

3) የክልሉ ሥራ ፈላጊዎች በተለይም ለወጣቶች እና ለሴቶች በስራ ፈጠራ ላይ በስፋት እንዲሰማሩ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ የስልጠና ድጋፍ፣ የመስሪያ ቦታ፣ ብድር፣ ገበያ ትስስር ምክር እና ሌሎች ድጋፎች እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ያመቻቻል።

4) የኢንተርኘራይዞች የድጋፍ ፓኬጅ ያዘጋጃል፣ ያቀናጃል፣ ያስፈጽማል፣ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል።

5) የማኑፋክቸሪንግ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ ላይ ለተሰማሩ ኢንተርኘራይዞች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ምርታቸውን ለውጭ ሀገር እንዲያቀርቡ ያግዛል።

6) የስራ ዕድል ፈጠራ ምክር ቤት በሁሉም ደረጃ እንዲቋቋም ያደርጋል፣ የምክር ቤቱን ስራ ያደራጃል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

7) የስራ ፈጠራ እና የስራ እድል ላይ ጥናት ያደርጋል፣ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ሲጸድቅ ስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል።

8) Hojji sektere widoonni kalaqantanno seedanna harancho yanna loosu kaayyo jeefishsha ha'runsitanno, irkissanno.
9) Hallanyu handaarira loosiisaanotenna loosaasinete xaadooshshe massagate fultino polisenna seerubba qoqqowu giddo loosu iima hosansa aliidimmatenni harunsitanno.
10) Loosiisaanotenna loosaasinete mereero heeranno lami-xaado hattono loosiisannote, loosaasinetenna mootimmate mereero heeranno sasi-xaado kaajishshanno loossa loosanno.
11) Loosu yekeero qaroomi'no garinni gumulo afidhanno gede irkisanno amuraatubba sirsitanno, jeefishshansano harunsitanno.
12) Seeru garinni fajjo afidhe qoqqowu giddo addi addi loosu handaarira bobbakkino baara widi qansoota borreessitanno, harunsitanno, loosu fajjonsa haaroo'mase buuxanno.
13) Addi addi mootimmate uurrinshshuwa giddonna mootimmatenni loosantanno addi addi pirojektubba widoonni kalaqantanno loosu kaayyo jeefishsha ha'runsitanno.
14) Qoqqowoho ikkitannota tekiniketenna ogimmate qajeelshi pirogiraamma gobboomu deerransa agadhite ha'ransa buuxxanno.
15) Deerrase agadhitino safoniti boodillaananna mereerima tekiniketenna ogimmate rosi qajeelshi kaarkuleeme qixxaabanno gede assitanno; ha'runsitanno; irkissanno.

8) በግሉ ሴክተር አማካይነት ሊፈጠሩ ስለሚገባቸው ዘላቂና ጊዜያዊ የሥራ ዕድሎች አተገባበር ይከታተላል፤ ይደግፋል፡፡
9) የግሉ ሴክተር የአሰሪና የሠራተኛ ግንኙነት ለመምራት የወጡ ፖሊሲዎች እና የሕግ ማዕቀፎች በክልሉ ተግባራዊ መሆናቸውን በበላይነት ይከታተላል፡፡
10) በአሰሪና በሰራተኞች መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት እንዲሁም በአሰሪ፣ በሠራተኛና በመንግሥት መካከል ያለውን የሦስትዮሽ ግንኙነትን የማጠናከር ተግባራትን ያከናውናል፡፡
11) የሥራ ክርክሮች በተፋጠነ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኙ የሚያስችሉ አሰራሮችን ይዘረጋል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፡፡
12) ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ አግኝተዉ በክልሉ በተለያዩ የሥራ መስኮች የሚሰሩ የዉጭ ዜጎችን ይመዘግባል፣ ይከታተላል፣ የሥራ ፈቃዳቸዉ መታደሱን ያረጋግጣል፡፡
13) በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ውስጥ እና በመንግስት በሚሰሩ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች አማካይነት የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች አፈጻጸም ይከታተላል፡፡
14) በክልሉ የሚከናወኑ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ፕሮግራሞች አገር አቀፍ ደረጃቸውን ጠብቀው መካሄዳቸውን ያረጋግጣል፡፡
15) ደረጃውን የጠበቀ መሰረታዊ መለስተኛና መካከለኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣

16) Qoqqowoho industiretenna investimentete millimmo irkissannota safonita boodillaananna mereerimu deerri tekinikete ogimma qajeelshu uurrinshuwa uurrissanno; halashshitanno; gashshitanno.

17) Tekiniketenna ogimmate rosinna qajeelshi kolleejuwanna hakko handaarira bobbakkannore wole qajeelshu uurrinshuwara balaxiafamooshshunna afamooshshu fajjoote uytanno; haaroonsitanno; deerru woroonni higge leelturo fajjootensa hooltanno.

18) Rosunna qajeelshunniha ogimmate ikkadimma buuxishshi amuraate qixxeessitanno; jeefishshasi ha’runsitanno; illaallissanno.

19) Konni handaarira hojji dureeyyenna mootimmaweelo uurrinsha beeqqitanno gara injeessitanno; jawaachishshanno; hasiissanno irko assitanno.

20) Qoqqowunnita tekiniketenna ogimmate rosinna qajeelshi istiraateeje qixxeessitanno; fajjiniro jeefissanno; jeefisiissanno.

21) Qoqqqowoho taalchunna farcamaanchu tekiniketenna ogimmate qajeelshi tuqishshi hee’ranno gede assitanno.

22) Dikkote hasatto mereersinoha rosaminonna rosaminokki qajeelshi pirogiraame roso qixxeessitanno; loosu aana hossanno gede assitanno; karikuleme qixxaabbanno raga leellishshanno.

23) Tekiniketenna ogimmate qajeelshi mereershuwa albillicho fulonsa uminsanni wonshi’ra

ይከታተላል፣ ይደግፋል።

16) በክልሉ የኢንዱስትሪና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴውን የሚያግዙ መሰረታዊ መለስተኛና መካከለኛ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል።

17) ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆችና በዘርፉ ለሚሰማሩ ሌሎች ማሰልጠኛ ተቋማት የቅድመ-ዕውቅናና ዕውቅና ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ከደረጃው በታች ሆነው ሲገኙ ፈቃዳቸውን ይሰርዛል።

18) የትምህርትና ሥልጠና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ያዘጋጃል፣ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

19) በዘርፉ የግል ባለሀብቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ያበረታታል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

20) የክልሉን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ ያዘጋጃል ሲፈቀድም ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል።

21) በክልሉ ተመጣጣኝ እና ፍትሃዊ የቴክኒክና ሞያ ስልጠና ሽፋን እንዲኖር ያደርጋል።

22) የገበያ ፍላጎት መሰረት ያደረገ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆነ ስልጠና መርሃ-ግብር ትምህርት ያዘጋጃል፣ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ስርዓተ ትምህርት የሚዘጋጅበት አቅጣጫ ይነድፋል።

23) የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት ወደ ፊት ወጪያቸውን በራሳቸው መሸፈን የሚያስችል

dandiissitannota eo lossate raga maltanno.

24) Tekiniketenna ogimmate qajeelshi uurrinshuwa gutoomunni qajeelsha uytanno assooti biddissa fushshitanno; jeefishshaho irkissanno; ha'runsitanno.
25) Qoqqowunnita sayinsetenna tekinoloojete hasatto baddanno, hajo la'annonsa bisubba ledo malamatenni hasatto wonshinanni gara injeessitanno.
26) Hajo la'annonsa bisubba ledo halamatenni qoqqowu giddo tekinoloojete paarke uurritanno gede assitanno.
27) Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole loossa jeefisiissanno.

**26. <u>Dagitte Owaantenna Mannu Jiro Latishshi Biiro</u>**

1) Qoqqowu mootimma loosaasine filatenna doorate lifinxe kaima ikkitanno gede assitanno, loosu deerrira hasiisanno roso, qajeelishanna loosu rosicho keenate xaphooma bikkancho qixxeesitanno, loosu aana hosiissanno.
2) Qoqqowu mootimma uurrinshuwa assitanno qixire, deerra lossate, base soorate, gaamate, qajeelshunna disippiliine dagate owaante seeri garinni jeefisamasi qorqortanno, assootu so'ro kalaqanturo taashshate qaafo adhitanno.
3) Qoqqowu mootimma loosaasine loosu guma keenate tittirshu biddissa fushshitanno, loosu aana hosiissanno, jeefisamasino ha'runsitanno.
4) Qoqqowu mootimma dagitte owaante lifinxaabbinotanna gummame ikkase buuxxanno.

የገቢ ማሳደግያየአፈፃፀም አቅጣጫ ይነድፋል፡፡

24) የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት በሽርክና ስልጠና የሚሰጡበትን የአሰራር መመሪያ ያወጣል፣ ለአፈፃፀሙ ይደግፋል፣ ይከታተላል፡፡
25) የክልሉን የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፍላጎት ይለያል፣ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመመካከር ፍላጎቱ የሚሟላበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
26) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ የቴክኖሎጂ ፓርኮች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፡፡
27) ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

26. <u>**የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ**</u>

1) የክልል መንግስት ሠራተኞች ምልመላና መረጣ በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደርጋል፣ ለስራ መደቦች የሚያስፈልጉ የትምህርት፣ የሥልጠናና የስራ ልምድ አጠቃላይ መመዘኛዎችን ያወጣል፣ ስራ ላይ ያውላል፡፡
2) በክልሉ የመንግስት መስሪያ ቤት የሚካሄድ ቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ ዝውውር፣ ድልድል፣ ሥልጠናና ዲሲፕሊንበፐብሊክ ሰርቪስ ሕግ መሰረት እየተፈፀሙ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፣ የአሰራር ስህተት ከተፈፀመ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡፡
3) የክልሉ የመንግስት ሰራተኞች የስራ ውጤት መመዘኛ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፣ በስራ ላይያዉላል፣ ተፈፃሚነቱ ይከታተላል፡፡
4) የክልሉ መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስ ብቃት

5) Dagitte owaantera mannu wolqa sufamino garinni latisatenna horo uytanno gede assate hayyo kalaqqanno, loosu aana hosase ha’runsitanno.
6) Dagitte owaante uytanori lifinxensanna loosu gummamimansa kaima assino baatoshshunna jawaachishate assooti loosu aana hosanno gede assitanno, gumaamimmasi keentanno, hasiisiro woyyeessate qaafo adhitanno.
7) Qoqqowu mootimma loosaasine akatoomme ha’runsate assooti loosu aana hosanno gede assitanno, jeefishshasi ha’runsitanno.
8) Qoqqowu mootimma loosaasine gashshootu seerubba garunni loosu aana hosansa ha’runsitanno, buuxxanno.
9) Mootimmate haandaari dhuka kaajjishate looso massagganno, mootimmate handaari owaante sufamino garinni woyyaabbannonna gummaame ikkitanno hayyo kalaqqanno, loosu aana hosase ha’runsitanno, keentanno.
10) Qoqqowu mootimma uurrinshuwa tantano gara ikkase xiinxallitanno, buuxxanno, tantano woyyeessate xiinxallo aana irko assitanno.
11) Qoqqowu mootimma uurrinshuwa mannu wolqa horonsi’nanni gara keentanno, woyyeessate hedo shiqishshanno, fajjiniro loosu aana hosase buuxxanno.
12) Qoqqowu mootimma uurrinshuwa owaante uynanni

ያለውና ውጤታማ መሆኑንያረጋግጣል።

5) የፐብሊክ ሰርቪሱ የሰው ኃይል በቀጣይነት በሚለማበት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል።

6) ለፐብሊክ ሰርቫንቱ በብቃትና በአፈጻፀም ውጤታማነት ላይየተመሰረተ የክፍያና የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይገመግማል አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ ይወስዳል።

7) የክልል መንግስት ሰራተኞች ሥነ-ምግባር መከታተያ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል።

8) የክልል መንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ሕጎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል።

9) የመንግስት ዘርፍ አቅም ግንባታ ስራዎችን ያስተባብራል፣ የመንግስት ዘርፍ አገልግሎት በቀጣይነት የሚሻሻልበትና ውጤታማ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል ተግባራዊነቱንምይከታተላል፣ ይገመግማል።

10) የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶችን አደረጃጀት አግባብነትን ያጠናል፣ ይመረምራል፣ በአደረጃጀት ማሻሻያ ጥናቶች ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፤

11) የክልሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን የሰው ሃይል አጠቃቀም ይገመግማል፣ ማሻሻያ ሃሳቦችን ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።

bikka, koffeenya shiqinshaninna tirranni amanyooti qixxaawasinna loosu aana hosasi buuxxanno.

13) Dagitte owaantera mannu jiro massagonna uurrinshate tajete amadooshshi suwashshonna kaajjado ikke loosamanno gede assitanno, mereerima tajete bue ikkite horo uytanno.

14) Qoqqowu mootimma uurrinshuwa mannu jiro gashshoote aliidimmatenni massagganno, loosu massago biddisuwanna jeefishshu bikkaancho qixxeessitanno, jeefisiissanno.

15) Mootimmate loosaasine damooza, barru hoshshonna addi addi aloowaanse woyyeessate xiinxallo assitanno, fajjiniro loosu aana hossanno gede assitanno.

16) Seeru garinni qoqqowu mootimma loosaasine xuratu diri gedensanni loosu aana keeshshiishate shiqqanno xa’mora gumulo uytanno.

17) Deerru deerrunkunni kalaqantanno danchu gashshootinna muishshu qarra badate xiinxallo, bandoonni rakko ajishate hayyo qixxeessitanno, rakko tirranni gara ha’runsitanno, irkissanno.

18) Horo bade afate xiinxallo assatenni mootimmate owaante aana dagate kassiimma buuxate looso loossanno.

19) Mootimmate loosaasine gashshooti yoo mine qineessitanno, garu seerinni massagamanno gede

12) በክልል መንግስት መስሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ፣ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፡፡

13) የፐብሊክ ሰርቪሱ የሰው ሃብት አመራርና የተቋማዊ መረጃዎችሥርዓት በወጥነት እንዲዳብርና እንዲተገብር ያደርጋል፣ማዕከላዊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡

14) የክልሉን የመንግስት መስሪያ ቤቶችን የሰው ሀብት አስተዳደር በበላይነት ይመራል፣ የስራ አመራር መመሪያዎችና የአፈፃፀም መስፈርቶችን ያዘጋጃል፣ ያስፈፅማል፡፡

15) የመንግስት ሰራተኞችን የደመወዝ፣ የልዩ ልዩ አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞች ማሻሻያ ያጠናል ሲፈቀድም ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

16) በሕግ መሰረት የክልል መንግስት ሰራተኞችን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ስለማቆየት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

17) በየደረጀው የሚታዩ የመልካም አስተዳደርና የኪራይ ሰብሳብነት ችግሮችን በጥናት መለየት፣ ለተለዩ ችግሮች ስልቶች በመንደፍ፣ የአፈታት ሂደት ይከታተላል፤ ይደግፋል፡፡

18) የፋይዳ ጥናት በማድረግ በመንግስት አገልግሎት ላይ የህዝብ እርካታን የማረጋገጥ ሥራን ይሰራል፡፡

19) የመንግስት ሠራተኞችን አስተዳደር ፍርድ ቤት ያደራጃል፣ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እንዲመራ ያደርጋል፡፡

assitanno.

20) Mootimmate owaantete handaara jawaachishate mittu mereerishi Owaante tantantanno, massaganno, irkkisanno;

21) Baxxino akati noonsa loosu minna aana xintante baxxitino damoozu isikeele xiinxallantanno gede mootimmatenni hajanjiro xiinxallite gashshootu amaale minira shiqishshanno, fajjinirono jeefishsha harunsitanno;

22) Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole hajubba jeefisiissanno.

**27. <u>Kominikeeshinete Biiro</u>**

1) Qoqqowu mootimmanna pirezidaantichu fooniixawisaancho ikkite loossanno.
2) Qoqqowu mootimma mashalaqqe mereershunni maareekkitenna qineessite hajo la’annonsa bisubbaranna miidiyaho hasiishshu bikkinni tuqissanno.
3) Qoqqowu mereershi sektere uurrinshuwa kominikeeshinetenna miidiyu xaadooshshi looso massagganno.
4) Qoqqowu mootimma dagate xaadooshshi looso loossanno, konforaanse, hasaawu battalanna ikkitubba qineesitanno.
5) Qoqqowu pirezidaantichinna mootimmate miidiyu xaadooshshi looso loossanno.
6) Gobba giddonna baara widi miidiyi odeessaanora hasiisanno bikkinni yanna yannatenni xawishsha uytanno.
7) Miidiya qorqoratenna tittirshu xawishsha qixxeessatenni mashalaqqe pirezidaantichahonna

20) የመንግስት አገልግሎት ዘርፍን ለማጠናከር የአንድ መዕከል አገልግሎት ያደራጃል፣ ይመራል፣ ይደግፋል፤

21) ልዩ ባህሪ ያላቸው የመ/ቤቶች ላይ ተመስርቶ ልዩ የደመውዝ እስኬል እንዲጠና በመንግስት ሲታዘዝ አጥንቶ ለመስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

22) ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**27. <u>የኮሚዩኒኬሽን ቢሮ</u>**

1) የክልሉን መንግስት እና የርዕሰ መስተዳድሩ ቃል አቀባይ ሆኖ ያገለግላል፡፡
2) የክልሉን መንግስት ኢንፎርሜሽን በማእከል አደራጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት እና ለሚዲያ እንደአስፈላጊነቱ ያሰራጫል፡፡
3) የክልሉ ማዕከል ሴክተር መስሪያ ቤቶችን የኮሚዩኒኬሽን እና የሚዲያ ግንኙነት ስራ ያስተባብራል፡፡.
4) የክልሉን መንግስት የህዝብ ግንኙነት ስራዎች ያከናውናል፤ ኮንፈረንሶች፣ ፓናል ውይይቶችን እና ሁነቶችን ያደራጃል፡፡
5) የክልሉን ርዕሰ መስተዳደር እና መንግስት የሚዲያ ግንኙነት ስራ ያከናውናል፡፡
6) ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ሚዲያ ጋዜጠኞች እንደየአስፈላጊነቱ በየወቅቱ መግለጫ ይሰጣል፡፡
7) የሚዲያ ሞኒተሪንግና እና ትንታኔ ስራ እያከናወነ መረጃውን ለርዕሰ መስተዳደሩ እና

hasiisanno bikkinni hajo la’annonsa bisubbara sayissanno.

8) Miidiyu ikkito aana xiinxallo assitanno, rippoorte qixxeessatenni pirezidaantichahonna hasiisanno bikkinni hajo la’annonsa bisubbara sayissanno.

9) Yanna yannatenni daga yaadisanno hajubba aana barrunna lamalate dagate hedo gamba assitanno, pirezidaantichahonna hasiisanno bikkinni hajo la’annonsa bisubbara sayissanno.

10) Jawa dagatenna mootimmate hajubbanna polise aana dagate lao xiinxallo assitanno, hajo la’annonsa bisubbara shiqishshanno.

11) Qoqqowu mootimma mashalaqqenna sokka sufamino garinni tuqissanno.

12) Mootimmate mashalaqqe webisayte fantanno, yanna yannatenni heedhanno mashalaqqe mootimmatenni loosamino loosonna jeefishsha hajo la’annonsa bisubbara iillitanno gede assitanno, ha’runsitanno.

13) Miidiyu bacihimma lopha jawaachishshanno, miidiyu mootimmatenna dagate mereero hee’rannosi loosu xaadooshshe massagganno, dagate xa’mo hajo la’anno mootimmate bissanni dawaro afidhanno gede assitanno, qara qara qoqqowunna gobbate deerrinni heedhanno ikkito hasiisanno miidiyu reqecco afidhanno gede injeessitanno.

እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡

8) የሚዲያ አዝማሚያ ጥናት ያከናውናል፤ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለርዕሰ መስተዳድሩ እና እንደ አስፈላጊነታቸው ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡

9) በየወቅቱ ህዝብን በሚያሳስቡ ጉዳዮች ላይ ዕለታዊ እና ሳምንታዊ የህዝብ አስተያየት መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ለርዕሰ መስተዳድሩ እና እንደ አስፈላጊነታቸው ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡

10) በትላልቅ የህዝብ እና መንግስት ጉዳዮች እና ፖሊሲዎች ላይ የህዝብ አመለካከት ጥናት ያከናውናል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፡፡

11) የክልሉን መንግስት መረጃ፤ ኢንፎርሜሽን እና መልዕክት በቋሚነት ያሰራጫል፡፡

12) የመንግስት የመረጃ ድህረ ገጽ ይከፍታል፣ በየጊዜው የሚገኘው መረጃ በመንግስት የተሰራ ስራና አፈፃፀም ወደሚመለከተው እንዲደርስ ያደርጋል፣ ይከታተላል፡፡

13) የሚዲያ ብዙህነት ዕድገት ያበረታታል፣ ሚድያ ከመንግስትና ከህዝብ ጋር የሚኖረው የስራ ግንኙነት ያስተባብራል፣ የህዝብ ጥያቄ አግባብ ባለው የመንግስት አካል ምላሽ እንዲሰጥበት ያደርጋል፣ ዋና ዋና ክልላዊና ሃገራዊ ፍፃሜና ኩኔት ተገቢው የሚዲያ ሽፋን የሚሰጥበት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

14) ለሚዲያና ለህዝብ ግንኙነት የሚያገለግል መመሪያ ያወጣል፣ በስራ ላይ መዋሉን

14) Miidiyahonna dagate xaadooshshi hajora hasiisanno biddissa fushshitanno, loosu aana hosasi ha'runsitanno.
15) Qoqqowunniha mashalaqqetenna kominikeeshinete looso federaalete mootimma loosi ledo qinaawino loosu xaadooshshenna waaxo kalaqqanno, jeefissanno.
16) Gobbatenna qoqqowu deerri mashalaqqe, kominikeeshinetenna miidiyu sektere polisenna seeru qoqqowu giddo loosu aana hosansa ha'runsitanno.
17) Federaalete egensiishshu seera kaima assatenni egensiishshu loosi lifinxe buuxisate taje uytanno, ha'runsitanno.
18) Qoqqowuniha dancha su'ma kaajjishate looso loossanno.
19) Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole hajubba jeefisiissanno.

**28. <u>Pilaanetenna Latishshu Biiro</u>**

1) Maakiro ikoonomete hanqafo qixxeessitanno, gashshootu amaale minira shiqishshe kajishshiishanno;
2) Qoqqowunnita seeda, mereerimanna harancho yanna mixo qixxeessitanno, jeefishsha ha'runsitanno, keentanno, rippoorte qixxeessatenni hajo la'annonsa bisubbara shiqishshanno.
3) Qoqqowu mootimma kappitaale pirojektubba hornyi xiinxallo assitanno, keentanno, kaajjishiishshanno.
4) Qoqqowu gashshootu taqqubba dirunnita jajju beehaachi afi'ri-mala qixxeessitanno, qoqqowu amaale minira shiqishatenni kaajjishiishshanno.

ይከታተላል፡፡

15) የክልሉን ኢንፎርሜሽን እና ኮሚዩኒኬሽን ስራ ከፌደራሉ መንግስት ስራ ጋር የሚያቀናጅ የስራ ግንኙነት እና ትብብር ይፈጥራል፤ ያስፈጽማል፡፡

16) አገራዊ እና ክልላዊ የኢንፎርሜሽን፤ የኮሚዩኒኬሽን እና የሚዲያ ሴክተር ፖሊሲዎች እና ሕጎች በክልሉ መተግበራቸውን ይከታተላል፡፡

17) የፌደራል የማስታወቂያ ህጎችን መሰረት በማድረግ የማስታወቂያ ስራ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤ ይከታተላል፡፡

18) የክልሉን ገጽታ ግንባታ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

19) ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**28. <u>ፕላንና ልማት ቢሮ</u>**

1) የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቅፍ ያዘጋጃል፤ ለመስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፡፡
2) የክልሉን የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፡፡
3) የክልሉን መንግሥት የካፒታል ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ያካሂዳል፤ ይገመግማል፤ ያስፀድቃል፡፡
4) በክልሉ ለታችኛው የአስተዳደር ዕርከን ዓመታዊ የሀብት ማከፋፈያ ቀመር ያዘጋጃል፣ ለክልሉ

5) Qoqqowunnita kappitaale pirojektubba jeefishsha ha’runsatenni keentanno, yannitte rippoorte qixxeessite hasiissanno bisubbara shiqishshanno.
6) Maakiro ikkonoomete polise jeefishshi xiinxallo ha’rissanno.
7) Qoqqowunnita latishshu xe’nenna latate dhuki xiinxallo assitanno.
8) Qoqqowinnita dagoomittenna miinju akati xiinxallo assitanno.
9) Qoqqowunnita mereerima yanna maakiro ikkonoomete hajo mamigeeshsha fayinaansete biro ledo halante qixxeessitanno, kaajjishiishshanno.
10) Qoqqowunita diru jiro geeshsha hedate taje qixxeessitanno፣ qoqqowu jeefisiisaanote amaale minira shiqishatenni kaajjishiishshanno.
11) Qoqqowunnita miinju, dagoomittenna baattote ofolla taje gamba assitanno, maarekkitanno, tittirsha qixxeessatenni horonsi’raanote tuqissanno.
12) Qoqqowunnita dagoomittenna miinju latishshi beehaachenna baattote ofolla xawissanno atilaasenna kaarta qixxeessitanno.
13) Qoqqowu mootimma uurrinshuwa loosinsa qeechinni qixxeessitanno istatistiksete taje gamba assitanno, maarekkitanno, tittirsha assatenni horonsi’raanote iillitanno gede assitanno, hattono deerrasinna silaanchimmasi agadhino garinni qixaawanno gede irko assitanno, ha’runsatenna qorqorate looso

ምክር ቤት እንዲጸድቅ ያቀርባል፡፡

5) የክልሉን የካፒታል ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤ ወቅታዊ ሪፖርት በማዘጋጀት አግባብነት ላላቸው አካላት ያቀርባል፡፡

6) የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አፈፃፀም ጥናት ያካሂዳል፡፡

7) የክልሉን የልማት ክፍተት እና የመልማት አቅም ጥናት ያደርጋል፡፡

8) የክልሉን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገፅታ ጥናት ያደርጋል፡፡

9) የክልሉን የመካከለኛ ጊዜ የማክሮ ኢኮኖሚ ከፋይናንስ ቢሮ ጋር ተናቦ ማዕቀፍያዘጋጃል፤ ያስፀድቃል፡፡

10) የክልሉን ዓመታዊ የሀብት ግመታ ሰነድ ያዘጋጃል፤ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል፡፡

11) የክልሉን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና መልክአ ምድራዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያደራጃል፤ ትንተና በማድረግ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፡፡

12) የክልሉን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማት ስርጭትንና የመልክዓ ምድራዊ ገፅታን የሚያሳይ አትላስና ካርታ ያዘጋጃል፡፡

13) የክልሉ መንግሥት መስሪያ ቤቶች በሥራቸው ኃላፊነት የሚያመነጩትን ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ እንዲሁም ስታንዳርዱንና ጥራቱን ጠብቆ እንዲዘጋጅ ድጋፍ፣ ክትትል እና ኦዲት

loosanno, tajete qorqorshi gumi kaiminni hasiissanno woyyeessate qaafo adhitanno.

14) Qoqqowunnita tajete foonqe taashshate xiinxallonna buuxote looso loossanno.

15) Qoqqowunnita istatistiksete taje amanyoote yannisate mootimmate uurrinshuwara irko uytanno, looso qineessitanno, massagganno.

16) Dagaallo hajubba latishshu mixo giddo amade jeefisa lainohunni mootimmannitinna mootimmaweelo uurrinshuwa massagganno.

17) Dagaallo hajubba lainohunni dagoomunna gashshootu bisubbara huwanyo kaajjishate kaa'litanno rosunna kakayishshu looso loossanno.

18) Dagaallo latishshu hajubba laainohunni xiinxallotenna buuxote looso loossanno.

19) Qoqqowunnita dagaallo polise loosu aana hosiisate, jeefisate kaa'litanno biddissubbanna maanuwalla fushshitanno.

20) Gashshootu taqqara heedhanno dagaallote amaale minna kaajjishatenna gutamaano bisubba qineessatenni ontu dirita dagaallote pirogiraame qixxeessitanno, dagaallote amaale minira shiqishshe kaajjishiishshanno, loosu aana hosase ha'runsitanno, keennanni raga wortanno.

21) Mixotenna pirojekte qixxeessa, ha'runsanna keena lainohunni dhuka kaajjishate looso loossanno.

ያደርጋል፣ በመረጃዎች አዲት ግኝት መሠረት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

14) የክልሉን የመረጃ ክፍተት ለማሟላት የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

15) የክልሉን የስታቲስቲክስ መረጃ ሥርዓት በማዘመንለመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ድጋፍ ይሰጣል፤ ሥራውን ያስተባብራል፤ ይመራል፡፡

16) የሥነ-ህዝብ ጉዳዮችን በልማት ዕቅድ አካቶ ከመተግበር አኳያ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያስተባብራል፡፡

17) በሥነ-ህዝብ ጉዳዮች የማህበረሰቡንና አመራር አካላትን ግንዛቤ ለማጎልበት የሚያስችሉ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎችን ያካሂዳል፡፡

18) የሥነ-ህዝብና ልማት ጉዳዮችን በተመለከተ የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፡፡

19) በክልሉ የስነ-ህዝብ ፖሊሲ ለመተግበር፣ ለአፈፃፀሙ የሚረዱ መመሪያዎች እና ማንዋሎች ያወጣል፡፡

20) በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙትን የሥነ-ህዝብ ም/ቤቶችን በማጠናከርና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የአምስት ዓመት የሥነ-ህዝብ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ለሥነ-ህዝብ ም/ቤቱ በማቅረብ ያፀድቃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይገመግማል አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

21) በዕቅድና ፕሮጀክቶች ዝግጅትክትትልና ግምገማ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

22) ከሚመለከታቸው የክልሉ የመንግስት አካላት

22) La'annonsa qoqqowu mootimma bisubba ledo buusamatenni seeda, mereerimanna harancho yannanni loosu aana hossanno waacantino pirojektuwanna pirogiraamma qixxaabbanno gede assitanno; fajjanturono loosu aana hosansa ha'runsitanno.

23) Maakirote miinji xiinxallo ha'rissanno; xiinxallote guma mootimmate shiqishshanno.

24) Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole hajubba jeefisiissanno.

**29. <u>Saadate Jiro Latishshi Biiro</u>**

1) Saadate jiro (mini saada, diida, qulxumenna wkl.) latishshi handaara halashshate kaa'litanno polise, istraateeje, seera qixxeessitanno, fajjinanni woyte loosu aana hosase ha'runsitanno, qorqortanno, jeefisanno.

2) Saadate jiro latishshi ekistenshiine paakeejje qixxeessatenni jeefissanno, jeefisiissanno, ha'runsitanno, ekistenshiinete ha'rinshono xiinxallotenni woyyaabbanno gede assitanno.

3) Qoqqowu giddo afamanno saadate sircho latishshu laayyonni baddanno, istiraatejike mixo qixxeessitanno, loosu aana hosiissanno, ha'runsitanno, qorqortanno.

4) Qoqqowu giddo laalichimasenninna xibba gargadhate dhukinni afantinore saadate sircho agarate haja la'anonsa bissa ledo halante loossanno.

5) Hegeraame ikkitino saadate sagale shiqo buuxisiisate

በመተባበር በረጅም፣ በመካከለኛ እና በአጭር ጊዜ የሚተገበሩ የተቀናጁ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ከተፈቀዱ በኋላም ተግባራዊ መሆናቸው ይከታተላል፡፡

23) የማክሮ ኢኮኖሚ ጥናት ያካሀዳል፣ የጥናቱ ውጤት ለመንግስት ያቀርባል፡፡

24) ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**29. <u>የእንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ</u>**

1) የእንስሳት ሀብት (የቤት እንስሳት፣ ንብ፣ ዓሣና ወዘተ.) ልማት ዘርፍን ለማስፋፋት የሚረዳ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ህጎችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስፈፀማል፡፡

2) የእንስሳት ሀብት ልማት ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን በማዘጋጀት ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣ ይከታተላል፣ የኤክስቴንሽን ሥረዓቱን በማጥናት እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡

3) በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ የእንስሳት ዝሪያዎችን በልማት ቀጠናዎች ይለያል፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ይተገብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

4) በክልሉ ዉስጥ ምርታማነታቸዉንና በሽታን በመቋቋም የታወቁ የእንስሳት ዝሪያዎችን ለመጠበቅ ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

5) አስተማማኝ የእንስሳት መኖ አቅርቦትን

woyyaabbino saadate sagale latishshi loossa loossanno, kalaqamu jiro latishshinna agarooshshi ledo qinaawe lattanno gede assitanno, qineessitanno.

6) Saadate laalchonna laalchimma lossinanni gibiaate shiqo injeessitanno, hala'litanno gede assitanno.

7) Qoqqowu deerrinni saadate xibbi qorqorshi isitiraateeje qixxeessitanno, jeefisiissanno, hasiise leelliro qaafo adhanno.

8) Gargarooshshe safo assino saadate fayyimma owaante uyitanno, saadate xibbi buuxo assanna qorqorshu loossa loossanno.

9) Keeraanchimmasinna isilanchimmasi agarantino maalinna saadate laalichi dagate shiqanno gede saada gorrinanni baycho maalu buuxo assitanno, deerra agarino saada gorrinanni mini baadiyyetenna quchummate minamanno gede ha'runsonna irko assanno.

10) Eeliidi tantanora saada xagisatenna kilinikete owaante uyitanno.

11) Saadatenna saadate laalichi latishshinna daddali, saadate xagishshi owaante aate bobbakkinorira fultinonna fultanno dandoote buuxishshi bikki garinni dandoote keeno assitanno, taje uyitanno, haaronsitanno, qinaambetenni ha'runsonna qorqorsha assitanno.

12) Qoqqowu giddo saadate daddali doogga baddanno, fooliishshote mereershi uurranno gede assitanno,

ለማረጋገጥ የተሻሻለ የመኖ ልማት ሥራዎችን ያከናውናል፣ ከተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ጋር አቀናጅቶ እንዲለማ ያደርጋል፤ ያስተባብራል።

6) የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ማሳደጊያ ግብዓት አቅርቦት ያመቻቻል፣ እንዲባዙም ያደርጋል።

7) ክልል አቀፍ የእንስሳት በሽታ ቁጥጥር ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ያስፈፅማል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝእርምጃ ይወስዳል።

8) መከላከልን መሰረት ያደረገ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ይሰጣል፣ የእንስሳት በሽታዎች ምርመራ፤ አሰሳና ቁጥጥር ሥራዎችን ያካሂዳል።

9) ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ የሥጋና የእንስሳት ተዋፅኦዎች ለህብረተሰቡ እንዲቀርቡ በቄራዎች የሥጋ ምርመራ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ደረጃቸዉን የጠበቁ ቄራዎች በገጠርና በከተሞች እንዲገነቡ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።

10) በተዋረድ ባሉ አደረጃጀቶች የእንስሳት ህክምና ክሊኒክ አገልግሎት ይሰጣል።

11) ለእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ ልማትና ንግድ ለእንስሳት ህክምናና ክልኒክ አገልግሎት ለሚሰማሩ አካላት በወጡና በሚወጡ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች መሰረት የብቃት ምዘና ያደርጋል፣ ማስረጃ ይሰጣል፣ በቅንጅት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል።

12) በክልሉ ዉስጥ የእንስሳት ንግድ የጉዞ መስመሮችን ይለያል፣ ማረፊያ ጣቢያዎች

kowaarantinenna qorqorshu mereershubba tantanatenni qoqqowu giddo, qoqqowunni fultannonna e’anno saadda qorqortanno, multanno qoqqowubbanna federaalete mootimma bissa ledo halamatenni loossanno.

13) Saadate laalchonna laalchimma lossinanninna woyyeessinanni gibiatta shiqo injeessitanno, qineesitanno.

14) Saadate Latishshiranna agarooshshira hasiissanno safote latishshuwa uurritannonna hala’litanno gede assitanno, aliidimmatenni massaganno, gashshitanno.

15) Saadate jiro latishshinni bobbakkinori loosidhenna allaa’lite galtinoriranna dureeyyete isilanchonna deerrase agadhitino saadanna saadate laalicho shiqishshanno gedenna owaante uytanno gede dhuka kaajjishate loosonna ogimmate irko assitanno.

16) Hajo la’annonsa mootimmatenna mootimmaame ikkitinokki bissa ledo halamatenni loossanno.

17) Qoqqowoho heedhanno saadate jiro latishshi taje yannilaancho doogonni gamba assitanno, maarekkitanno, fatilsitanno, horote aana hosanna gede assitanno.

18) Saadate jiro latishshinni leelitanno dancha rosichuwa gamba assite maarekkatenni wole qooxeessuwara hala’litanno gede assitanno.

19) saadate jiro latishsha lainohunni giwirinni xiinxallo inistitiyutenni loosantanno xiinxawo aliidimatenni

እንዲቋቋሙ ያደረጋል፣ የኳራንታይንና የፍተሻ ማዕከላትን በማደራጀት በክልሉዉስጥ፤ ከክልሉ የሚወጡና የሚገቡ እንስሳትን ይቆጣጠራል፣ ከአጎራባች ክልሎችና ከፌዴራል መንግስት አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

13) የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ማሳደጊያና ማሻሻያ ግብዓቶች አቅርቦት ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፡፡

14) የእንስሳት ሀብት ልማትና ጥበቃ የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶች እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ በበላይነት ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡

15) በእንስሳት ሀብት ልማት ለተሰማሩ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ባለሀብቶች ጥራትና ደረጃዉን የጠበቀ እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦ እንዲያቀርቡና አገልግሎት እንዲሰጡ የአቅም ግንባታ ሥራና የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

16) ከሚመለከታቸዉ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

17) የክልሉን የእንስሳት ሀብት ልማት መረጃ በዘመናዊ መልኩ ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ እንዲዉል ያደርጋል፡፡

